# የማኅሌተ ጽጌ ትርጉምና ታሪክ

## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ የታየ እና የተመረመረ
## ክፍል ሦስት ሁለተኛ እትም



አባእኩ ለኪ ስብሐተ ተአምር
“ማርያም ሆይ ድንቅ ተአምር ያለበት
ምስጋናን አቀረብኩልሽ” ገጽ 51
ትርጉም ሊቀ ጠበብት አስራደ ባያብል ሰኔ 21 ቀን ፳፻፭ (2005) ዓ.ም
አዘጋጅ ይርጋለም ወሰኑ
አዲስ አበባ

# የማኅሌተ ጽጌ ትርጉምና ታሪክ፡፡

## ክፍል ሦስት

### ሁለተኛ እትም

### አብእኩ ለኪ ስብሐተ ተአምር

"ማርያም ሆይ ድንቅ ተአምር ያለበት
ምስጋናን አቀረብኩልሽ"

ገጽ 51

ትርጉም ሊቀ ጠበብት አስራደ ባያብል

አዘጋጅ ይርጋለም ወሰኑ

ዓለም አታሚዎች ታተመ
አዲስ አበባ
ሰኔ 21 ቀን
፳፻፭ (2005) ዓ.ም፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ያለ ተርጓሚውና ያለ አዘጋጁ ፈቃድ፣ መልሶ ማሳተምና ማባዛት፣ በሕግ የተከለከለ ነው።

## መግለጫ

ማኅሌተ ጽጌ በተባለ መጽሐፍ ውስጥ በሚገኙ የግእዝ ስንኞች ላይ አልፎ አልፎ የንባብ ልዩነት ይታያል። ይህም የቃላት ልዩነት እንጂ የትርጉም፣ የምሥጢርና የታሪክ ልዩነት የለም፣ የመጽሐፉ አዘጋጃጀትም በበአታ (በታች ቤት) የሚባለውን ቀለም እያስቀደመ፣ በግምጃ ቤት (በላይ ቤት እና በተለያዩ አድባራት የሚባለውን ቀለም) ደግሞ፣ በቅንፍ እያደረገ የተዘጋጀ መሆኑን ከወዲሁ እንጠቁማለን። ‹‹ለምሳሌ›› ገጽ 6 ጠቢ.ብከ. (ጠቢብሰ) የሚለውን ከተራ ቍጥር (103) 3ኛውን ስንኝ መመልከትና ሁሉንም በዚህ መረዳት ይቻላል።

አድራሻ:- ☎ 09 21 64 64 29
09 13 28 83 74

የሕይወትዎ ማስታወሻ !!

ከ..........................................................................

ለ ..........................................................................

ቀን...............................................ዓ.ም............

## መታሰቢያነቱ

«በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን ለትርጓሜ መጻሕፍት፣ ለቅኔ፣ ለአምስቱ ፀዋተወ ዜማ መምህራን፣ ለስብከተ ወንጌል፣ ለሰባክያነ ወንጌል እና ለኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/ሰ/ት/ቤቶች ይሁንልን።

## ምስጋና

- ይህ መጽሐፍ፣ ለቤተ-ክርስቲያን አስፈላጊ መሆኑን አምኖበት ለሥራው ቅድሚያ በመስጠት፣ በሊቃውንት ጉባኤ እንዲመረመር ላደረገ ለመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት፣
- መጽሐፉን፣ በተደጋጋሚ መርምሮና አስተካክሎ ለኅትመት እንዲበቃ ላደረገ፣ ለኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ፣
- መጽሐፉን፣ በግል ተመልክተውና ሊያዩትም ይገባል፣ ብለው ላመኑባቸው ሊቃውንት፣ ላስመረመሩ፣ ለዶ/ር አባ ኃይለ ማርያም መለሰ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተክህነት የስብከተ ወንጌል መምሪያ ዋና ኃላፊ፣
- ጊዜውን መሥዋዕት አድርጎ፣ መጽሐፉን መርምሮ ለኅትመት እንዲበቃ ላደረገ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን በሰ/ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ለማኅበረ ቅዱሳን፣መጻሕፍት ምርመራ ክፍል፣

በኮምፒዩተር ጽሑፍ ለተባበሩን እኅቶች:-

- ለወ/ሮ አቡና ታከለ (ወለተ ማርያም) ከወሎ ላስታ ላሊበላ፤
- በጽሑፍ ደረጃ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትል ክፍል ሁለትን እና ክፍል ሦስትን ለኅትመት ላበቃች ወጣት እመቤት ደምሰው ከአዲስ አበባ ደብረ ገሊላ አማኑኤል ካቴድራል

- ለወጣት ትርሐስ ሺሻይ (ወለተ መስቀል) ከምዕራብ ትግራይ ሽሬ እንደሥላሴ ከተማ፤ በተለይም ይህ መጽሐፍ፣ ለኅትመት እስከበቃበት ድረስ የኮምፒዩተር ሙሉ እገዛ ላደረጉልን ለአቶ አካሉ ቢረዳ (ወልደ ጊዮርጊስ እና) ለባለቤታቸው ለወ/ሮ ፀሐይ ወልደ ሐዋርያት (ወለተ መስቀል) ከጉራጌ ምሁር፣
- ለሻምበል መንግሥቱ ለገሰ ከጅጅጋ፣ በጠቅላላ በተለያየ መልኩ ለረዱን ሁሉ እግዚአብሔር አምላክ መልካም ጤናንና ረጅም ዕድሜን ይስጥልን።

ትርጉም፦ ሊቀ ጠበብት አስራደ ባያብል፣

አዘጋጅ፦ ይርጋለም ወስኑ።

www.ethiopianorthodox.org

## ማውጫ

ገጽ

1. ልብስና ወንበር፣ ደግና ክፉን ስለመለየታቸው............... 7
2. በወላጆቹ ቤት (15) ዓመት ሲኖር ያልታወቀ ሙሽራ...... 8
3. መንግሥቱን ንቆ የመነነው ድንግል ንጉሥ...................... 9
4. በሞት የተለወጠ (በሃይማኖት ጽናት የተገኘ) የክህነት መዓዛ................................................................. 10
5. እመቤታችን ከንፍረትና ከጭንቅ እንደምትታደግ............ 12
6. የተቀበረ ወርቅ ጌታውን ስለ ማቃጠሉ......................... 14
7. የአውሎጊስ ነፍስና የዳንኤል ስቅለት........................ 18
8. በእመቤታችን ቃል ኪዳን ስምዖን ስለመዳኑ................ 20
9. መብራትን አጥፍቶ ሲገረፍ ስላለቀሰ ሰይጣን............... 21
10. እስራኤል በልብሳቸው ጫፍ ስለ አደረጉት ምልክት...... 22
11. የአውሬ ዓይኑን የሚወጋ ዕንቊሽን በመስቀል ምልክት ሣዒብኝ ለምን አለ?.......................................... 22
12. ሐዋርያትና በሲኦል የነበሩ ነፍሳት መቼ ተጠምቀው ነው! ሥጋውንና ደሙን የተቀበሉ?............................... 27
13. ከሥዕል ጡቶች የፈለቀው ዘይትና ሜሮን................. 28
14. ጥምቀት ወደ ኢትዮጵያ እንዴትና መቼ መጣች?....... 28
15. የእመቤታችን ሥዕል በጼዴንያ ድምጽ ማሰማት ......... 30
16. ከተቈረጠችው ሥዕል የተሰማው ድምጽ.................. 31
17. የእመቤታችን ሥዕል፣ በንብ ቀፎ ውስጥ ስለመታየቷ........ 33
18. ዮሐንስ፣ ዳንኤልና አፈወርቅ እንዴት ተባለ?.................. 36
19. ምድራዊው፣ ሰማያዊውን ስለ መርዳቱ..................... 39
20. የሞቱና ያልሞቱ ሰዎች በዓይን ስለመተያየታቸው....... 40
21. አንበሳ ውሃን ስለመቅዳቱ........................................ 42
22. ሰይጣን ድንጋይን ስለ መሸከሙ................................ 42
23. እመቤታችን በርግብ አምሳል በጊዮርጊስ ቤት............ 43
24. ቤተክርስቲያን ለመጀመሪያ ጊዜ በየት ተሠራች?.......... 45
25. በዓለም የመጀመሪያው ጸሐፊ ማን ነበር?..................... 46
26. እመቤታችንን የሕጻናት ምስጋናን አሰሚኝ ስለምን አለ?... 47
27. ጌታ የባረካቸው ሕጻናት ምን ሆኑ?........................... 47
28. ጌታ የታቀፈው ሕጻን ስሙ ማነው?............................ 48
29. አንበሳ መቃብሯን ስለ ቆፈረላት ደሃ.......................... 51
30. ፊደል መቼና በማን መጣ? ፊደል ማለትስ ምን ማለት ነው?............................................................ 54
31. (22ቱ) አርእስተ አበው የሚባሉ ማን ማን ናቸው?....... 55
32. ፊደል ስለነበራቸው እና ስላልነበራቸው ቋንቋዎች........ 57
33. ቅዱስ ኤፍሬም የድንግል ማርያምን ውዳሴ መቼ ደረሰ?... 60
34. ዋቢ መጻሕፍት.................................................. 62-64

www.ethiopianorthodox.org

፪፡-102 ኦ፡ ረዳኢተ ድኩማን ዘይረድአኪ ኢተኀሥሢ፣
እመንበረ ላዕክኪ በምዕር ከመ ገፍታዕኪዮ ለወራሲ፣
ለገፍትዖ ፀርየ ድንግል ኃይለ ዚአኪ ልበሲ፣
ዘይሳለቅ ተአምረኪ እንዘ ሐሰተ ይሬሲ፣
መፍትውኑ ከመ ይሕየው ከይሲ፡፡

*የሚረዳሽ የማትፈልጊና የድኩማን ረዳት የሆንሽ ጽዮን የተባልሽ ድንግል ሆይ ኃይልሽን ልበሺ (ግለጪ) ተብሎ ትንቢት እንደተጻፈ ኢሳ.52.1. ከአገልጋይሽ (ከደጉ ደቅስዮስ) ወንበር ላይ የተቀመጠ ወራሽን (ትዕቢተኛው ደቅስዮስን) በአንድ ጊዜ እንደገለበጥሽው ጠላቴ ሰይጣንን ለመገልበጥ ኃይልሽን ልበሺ (ተአምርሽን አሳዩ)፣ ተአምርሽን ውሸት ነው ብሎ በተአምርሽ የሚዘባበት ሰው ሔዋንን ያሳተ እባብ ነውና፣ (ዘፍ. 3 14-16፣ ኢሳ.27.1-2) በሕይወት ሊኖር ይገባዋልን?፡፡*

፻፫፡-103 ለተአምርኪ ማርያም ዓብድ ውእቱ ዘገደፎ፣
እስመ ገደፍኪዮ ሎቱ ወጽጌ ደመና ኀሊፎ (ኀለፎ)፣
ጠቢብኬ (ጠቢብሰ) ለተአምርኪ ዘአጽሐፎ (ዘጸሐፎ)፣
እንዘ እምኀቤኪ ነሚአ ዕሤት ይሴፎ፣
ተዘኪሮ ለደቅስዮስ አጽፎ፡፡

*ማርያም ሆይ ተአምርሽን የናቀ ሰው ሰነፍ (አላዋቂ) ነው አንቺ እርሱን ጥለሽዋልና፣ የደመና አበባም (ተድላ ደስታ) አልፎበታልና (አልፎታልና) ደቅስዮስ ከአንቺ ዘንድ ያገኘውን ዋጋ አገኛለሁ ብሎ አስቦ የሚታመን እና ተአምርሽን ያስጻፈው ግን ብልህ ነው! (ጠቢብስ ተአምርሽን የጻፈ ነው)፡፡*

፻፬፡-104 ሶበ ጸሐፈ ደቅስዮስ ተአምረኪ ቅዱሰ፣
መንበረ ወአፅፈ ዕሤተ ጻማሁ ወረሰ፣
ማርያም ድንግል ዘታብዕሊ ጽኑሰ፣
ዓስበ ማኅሌትየ አቅመ ልብየ ኀሠሠ፣
ጸግውኒ አትሮንስ ወጽጉየ ልብሰ፡፡

(1) ዲያብሎስን፣ ከአራዊት ሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እና ዘፍ.3.1-3 መርዝ በጥርሱ ያለው ከይሲ (እባብ) ጥበ.16.10 በተባለው አውሬ ስም ማን ጠራው? →



*ደሃውን ባዕለጸጋ (ኃጥኡን ባለ ተስፋ) የምታደርጊ ድንግል ማርያም ሆይ ደቅስዮስ፣ ልዩ ተአምርሽን በጻፈ ጊዜ የድካሙ ዋጋ (የጽድቅና የክብር መገለጫ) የሆነ ልብስንና ወንበርን አገኘ ልቡናዬ በፈለገ መጠንም የምስጋናዬ ዋጋ የሆነ ወንበርንና አበባ የመሰለ ልብስን ስጪኝ፣ (በምድር በረከትን ሰጥተሽ የጻድቃን ርስታቸው የሆነች መንግሥተ ሰማያትን አድዪኝ)፡፡* በተራ ቍጥር 102፤ 103 እና 104 ያሉ ታሪኮች የአንድ ተአምር ታሪኮች ስለሆኑ ታሪካቸው በዚህ በተራ ቍጥር 104 ላይ ተካቷል፡፡

## ልብስና ወንበር ደግና ክፉን ስለመለየታቸው

(ታሪክ) ጥልጥልያ በምትባል አገር በእመቤታችን ስም በተሠራች ቤተ ክርስቲያን በቅንነት የሚያገለግልና ስሙ ደቅስዮስ የሚባል ደግ ኤጲስቆጶስ ነበር፣ እመቤታችንንም ከመውደዱ የተነሣ ተአምሯን የሚናገር መጽሐፍን ሁሉ ከየአገሩ ሰበሰበ እመቤታችንም ተገልጻ፣ መጽሐፍን ይዛ አይቶ ደስ አለው፣ እሷም የአገልግሎትህን ዋጋ እሰጥሃለሁ ብላ ማንም ያልለበሳት ልብስና ማንም ያልተቀመጠባት ወንበርን ሰጠችው፣ ልብሷንም ማንም ሊለብሳትና በወንበሯ ማንም ሊቀመጥባት አይችልም ከአለችው በኋላ ከእሱ ተሠወረች፡፡ ይህ ደጉ ደቅስዮስም ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ሌላ ደቅስዮስ ተሾመና በትዕቢት ተነሳስቶ እኔም እንደ እርሱ ኤጲስቆጶስ ነኝና ልብሷንም ልልበስ፣ በወንበሯም ልቀመጥ ብሎ ልብሷን ለብሶ በወንበሯ ላይ ሲቀመጥ፣ መታበይን (ኩራትን) የሚንከባከባት ሰው፣ እሳትን ያነድዳታል (ኃጢአትን ያበዛታል) ብሎ መጽሐፍ እንደተናገረ ሲራ.28.11-13. ከቤተ ክርስቲያን በመጡ በምእመናን ፊት ከወንበሯ ላይ ተገልብጦ ሞተ (የታኅሣሥ 29 ቀን መጽሐፈ ስንክሳር እና 1ኛ ተአምረ ማርያም)፡፡

(2) ዲያብሎስ፣ አዳም በገነት ሳለ የሰማይና የምድር ንጉሥ አዳም ሆይ ሲለው አዳም፣ ከንቱ ውዳሴን ባለመቀበል ስምህ ከይሲ (እባብ) ይሁን ብሎ ጠራው፣ (የዓርብ መጽሐፈ አክሲማሮስ ክፍል አራት)፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ጀ፩፥-105 ለተአምርኪ ማርያም ኃጥእ ውእቱ ዘአስተቶ፣
ከመ ስብሐቲሁ ኢይርአይ እስመ ጽጌኪ አእተቶ፣
ለተአምርኪሰ እንዘ ይነግር ረድኤቶ፣
ቦ ዘፈለሰ ኅዲጎ ብእሲቶ፣
ወቦ ገዳመ ዘተግሕሠ (ዘወፈረ) መኒኖ መንግሥቶ::

ማርያም ሆይ ተአምርሽን ያቃለለ ሰው ኃጥእ (በደለኛ) ነው የጌትነቱን ክብር እንዳያይ ልጅሽ አስወግዶታልና:: ነገር ግን የተአምርሽን አጋዥነት እየነገረ ሚስቱን ትቶ የመነነ አለ (ነበረ)፣ መንግሥቱንም ንቆ ወደ ገዳም የገባ አለ::

## በወላጆቹ ቤት (15) ዓመት ሲኖር ያልታወቀ ሙሽራ

(ታሪክ) ቍስጥንጥንያ በምትባል አገር የነገሠ ቴዎዶስዮስ፣ ሚስቱም ማርኬዛ (መርኬዛ)፣ ጌታን የሚፈሩ ሲሆኑ ልጅ አልነበራቸውምና፣ ኢየሩሳሌም ሄደው ተስለው ልጅ ወለዱ፣ ስሙንም አብደል መሲሕ ብለው ጠሩት ትርጕሙም ገብረ ክርስቶስ (የክርስቶስ አገልጋይ) ማለት ነው የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት አስተምረው በተወለደ (በ20) ዓመቱ የሮሜን ንጉሥ ልጅ እንደ ሥርዓቱ አጋቡት መንፈቀ ሌሊት ሲሆንም የሙሽራዋን እጅ ይዞ ነአምን በአሐዱ አምላክ (በአንድ አምላክ እናምናለን) የሚለውን የሃይማኖት ጸሎት እስከ መጨረሻው ጸልዮ እና ጌታ ከአንቺ ጋር ይሁን ከሰይጣንም ሥራ ያድንሽ ብሎ ተሰናብቷት አርማንያ ወደምትባል አገር ሄዶ በእመቤታችን ስም በተሠራች ቤተ ክርስቲያን ጥግ በሰንበት ቀን ብቻ እህልና ውሃ እየቀመሰ በጾምና በጸሎት እየተጋደለ (15) ዓመት ኖረ ከዚህ በኋላም ይህ ወጣት በወላጆቹ ቤት ልጃቸው እንደሆነ ሳይታወቅ (15) ዓመት ኖሮ በጠቅላላ (ከ30( ዓመት ተጋድሎ በኋላ ጥቅምት (14) ቀን በተወለደ (በ50) ዓመቱ ዐረፈ (የጥቅምት 14 ቀን መጽሐፈ ስንክሳር እና 170 ተአምር)::

(3) ትዕቢት ከአለች ዘንድ ውርደት አለችና፤ ልጅ ሆይ በባለእንጀራህ ላይ ልቡናህን አታኩራ መጽ.ጦቢ.4.13-14::



## መንግሥቱን ንቆ የመነነው ድንግል ንጉሥ

በሮም አገር ስሙ ማርቆስ የሚባል ደግና ድንግል ንጉሥ ነበር በመልካም ሥነ ምግባርና በሃይማኖት ጸንቶ (10) ዓመትን ከፈጸመ በኋላ የሮም መኳንንት ሴትን እንዲያገባ ለመኑት ንጉሡም ለእመቤታችን እስክነግራት ድረስ (ለ7) ቀን ያህል ታገሡኝ አላቸውና በእመቤታችን ሥዕል ፊት ቆሞ ሲጸልይ የሥዕሏን ብርሃን አይቶ እያደነቀ ሳለ ንጉሥ ሆይ ይህ ዓለም ለአንተ አይደለም እናንተስ አስቀድማችሁ የጌታን መንግሥቱንና ጽድቁን ፈልጉ ተብሎ እንደተጻፈ (ማቴ 6. 33) ሰማያዊ መንግሥትን መርምር እንጅ አለችው:: ንጉሡም በዚህ ምክንያት ማንም ሰው ሳያየው ምድራዊ መንግሥቱን ንቆ ሰማያዊ መንግሥትን ወደሚወርስባት ቶርማቅ ወደ ምትባል ገዳም ሄዶ (60) ዓመት በጾምና በጸሎት ተወስኖ ኖሯል የሰኔ (29) ቀን መጽሐፈ ስንክሳር እና 201 ተአምረ ማርያም):: የኢትዮጵያ ንጉሥ አፄ ካሌብም እንደ ንጉሥ ማርቆስ መንኖ ወደ ገዳም ሄዶ (12) ዓመት በጾምና በጸሎት ተወስኖ ኖሮ በ538 ዓ.ም ግንቦት (20) ቀን በክብር ዐርፏል (147 ተአምረ ኢየሱስ እና 255 ተአምረ ማርያም) ::

ጀ፮፥-106 ተአምርኪ መጽሐፈ ጽጌ በኀቤየ ክቡር፣
ከመ ወንጌሉ ቅዱስ ለሕፃንኪ ፍቁር፣
ጽላተ ኦሪት ማርያም ጸዋሪተ ትእዛዝ ዐሥር፣
እምይደቅ እምቃልኪ አሐዱ ነገር፣
ይቀልል ኅልፈቶሙ ለሰማይ ወምድር::

ዐሥሩ ትእዛዛት የተጻፉባት የኦሪት ጽላት ዘጸ.31.18 ምሳሌ የሆንሽ ማርያም ሆይ ተወዳጅ እንደሆነ እንደ ልጅሽ ቅዱስ ወንጌል፣ ደስ የሚያሰኝ ታሪክን የያዘ ተአምርሽ በእኔ ዘንድ የከበረ ነው፣ ከቃልሽም አንዱ ነገር ከሚወድቅ የሰማይና የምድር ማለፍ ይቀላል:: ቅዱስ ሉቃስ (ከ72ቱ) አርድእት አንዱና የድንግልና ሕይወት የነበረው፣ የሥዕልና የሕክምና ባለሙያ ሲሆን ፣ ከአራቱ ወንጌል አንዱን ወንጌልና

(4) ብዙ ሰዎችን የልቡናቸው ትዕቢት በመከራ ጥሏቸዋልና፤ የትዕቢትን ነገር እንዳትናገር እወቅ ሲራ 3.23፣ 35.12::

www.ethiopianorthodox.org

*የሐዋርያት ሥራ የተባለውን መጽሐፍ ጽፎ በተወለደ (በ84) ዓመቱ በ68 ዓ.ም ጥቅምት (22) ቀን ያረፈ የክርስቶስ አገልጋይ ነበር ሉቃ. 1. 1-5፣ የሐዋ. 1. 1-3፣* ቆላ 4.14 *ገድለ ሐዋርያትና የጥቅምት (22) ቀን መጽሐፈ ስንክሳር::*

(ሙሴ ጽላትን ከጌታ የተቀበለ ዓለም በተፈጠረ በ3844 ዓመት ነው) ዘጸ 31.18::

ጀ፺፯፡-107 ተአምርኪ መጽሐፈ ባሕርይ ዘአፀወ ቀዳሚ፣
አፈ ዕጉሥታር አርዌ መምህረ አይሁድ ወአረሚ፣
መዓዛ ጽጌያት ጥዕምት እምዔና ልብሱ ለአበ ብንያሚ፣ (ለአባ ብንያሚ)፣
ለፀርኪ መሪረ አፍ ወምሉአ መርገም ሳሚ፣
በተአምርኪ ማርያም ልሳኖ አብሕሚ::

*ማርያም ሆይ አምላክ ሰው ሆነ፣ ሰው አምላክ ሆነ የሚለውን ነገረ ሥጋዌ (የአምላክ እናት መሆንሽን) ማቴ.1.22-24፣ዮሐ.1.14-15፣ ክዶ አንደበቱ እንደ እሬት የመረረ የአይሁድና የአረማውያን መምህር የሆነ የንስጥሮስ አንደበትን አስቀድሞ የዘጋ ተአምርሽ፣ ብንያሚን በሚባል ካህን አባት ሕመም ምክንያት ከተገኘ ከአባ ብንያሚን የልብስ መዓዛ ይልቅ፣ እንደ አበባ መዓዛ የጣፈጠ (ደስ የሚያሰኝ) ነው:: አንደበቱ መራራ የሆነና ሳሚ እንደሚባለው ሰውም፣ 2ኛ ሳሙ. 16፥5-15. እርግማንን የተሞላና የተአምርሽን ጠላት በተአምርሽ አንደበቱን ዝጊ (ዲዳ አድርጊ)::*

## *በሞት የተለወጠ (በሃይማኖት ጽናት የተገኘ) የክህነት መዓዛ*

(ታሪክ) በግብጽ ደቡብ ቱና በሚባል አገር የቤተ መቅደስን ሥርዓት አውቆ፣ ክህነቱንም ጠብቆ የሚኖር ብንያሚን የሚባል አንድ ካህን ነበር ከዕለታት አንድ ቀን ቤተ መቅደስ ገብቶ ልብሰ ተክህኖ ከለበሰ በኋላ አባትህ ታሞ ሊሞት ቀርቧልና እርሱን (አንተን) አምጡልኝ ብሏል ቢሉት፣ ቀሲስ ብንያሚን ግን የቍርባኑን ሥርዓት ሳልፈጽም ልብሰ ተክህኖውን አላወልቅም፣ እግዚአብሔር ከፈቀደ ሳይሞት ይቆየኛል፤ ካልፈቀደ ግን ጌታ እንደ ወደደ ይሁን ብሎ የእግዚአብሔርን ሥርዓት ፈጸመ:: በዚህ ምክንያትም የአባ

(5) የሰነፎች ምላስ ስንፍናን ይራገራል፤ የጠቢባን ምላስ ግን እውቀትን ትዘራለች ምሳ 15.2-7::



ብንያሚን ክህነት፣ እንደ መልከጼዴቅ ክህነት የተባረከ ሆኖ፣ ዘፍ.14.18-20፣ መዝ.109.4፣ ዕብ.7.16-18. ልብሱ እጅግ ልዩ መዓዛ የነበረው ካህን ነበር (የሐምሌ (1) ቀን መጽሐፈ ስንክሳር):: (ጥቅስ) አንትሙሰ ከመ እብነ ሕይወት ተሐነፁ ቤቶ ለመንፈስ ቅዱስ፣ "እናንተስ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሥዋዕትን ታቀርቡ ዘንድ ቅዱሳን ካህናት እንድትሆኑ፣ የመዓዝን ራስ ሆኖ እንደከበረ ድንጋይ መዝ.117.22. መንፈሳዊ ቤትን ለመሆን ተሠሩ" የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል 1ኛ.ጴጥ.2.6 በሥርዓቱ ከፈጸመ ከካህኑ ከብንያሚን ልብሰ ተክህኖ ልዩ ተአምር ታየ ይህንንም ቃል ቅዱስ ያሬድ ዝማሬ በተባለ ድርሰቱ ወስዶታል::

ጀ፻፰:-108 ተአምርኪ መጽሐፈ ሕይወት እሞት ዳግም፣
ምዕዳወ ሲኦል ወሞት ዘውእቱ ገሀነም፣
ታሕይውኒ ቦቱ ሕይወተ ኲሉ ዓለም፣
ተማሕጸንኩ ለጽጌ ከርሥኪ ጊዜ ረከቦ ሕማም፣
በዘአገቱኒ ሰቆቃው ወአንብዐ መስጥም::

*የዓለም መድኀኒት የሆንሺ ማርያም ሆይ የሲኦልና የሞት መሸጋገሪያ በሆነውና ሕይወት (የሥላሴ ፈቃድ) ባለበት ተአምርሽ፣ ዳግም (ሁለተኛ) ሞት ከተባለው ከገሃነም ሞት፣ ራእ. 20.11-15. ታድኚኝ ዘንድ የማሕፀንሽ ፍሬ የሆነ ልጅሽን መከራ በአገኘው ጊዘ በከበቡሽ ልቅሶና በሚያሰጥም ዕንባ ተማጸንኩ::*

ጀ፻፱፡፡-109 መልዐ ተአምርኪ ኲሎ መካነ፣
አድባረኒ በሥነ ጽጌሁ ከደነ፣
ማርያም ፍሥሓ ዘታረስዒ (ዘትሥዕሪ) ኀዘነ፣
በከመ አውጻእኪ እምከርሠ እመ ምኔት ሕፃነ፣
እሞተ ኃጢአት ነፍስየ አውፅኢ ፍጡነ::

*ኀዘንን ሽረሽ (አስረስተሽ)፣ ደስታን የምትሰጪ ማርያም ሆ ተአምርሽ፣ ቦታውን ሁሉ ሞላ፣ ተራራዎችንም በአበባው ውበ ሸፈነ፣ ከእመምኔትዋ (የሴቶች ገዳም አለቃ ከሆነች) ማሕፀን ሕፃኑ እንደአወጣሽ ነፍሴን ከኃጢአት ሞት ፈጥነሽ አውጪ::*

(6) ጠቢብ (አዋቂ) ንጉሥ፣ ሰራዊቱን ይመክራል፤ ሥርዓትንም ይሠራል ሲራ 10.1-2::

www.ethiopianorthodox.org

## እመቤታችን ከኀፍረትና ከጭንቅ እንደምትታደግ

(ታሪክ) ቀርሜሎስ በሚባል ገዳም እመቤታችንን የምትወድ ሶፍያ የምትባል እመምኔት (የሴቶች ገዳም አስተዳዳሪ) ነበረች በገዳሙ ውስጥ በድንግልና ለሚኖሩ ብዙ የሴት መነኮሳትም የቀኖናን ሥርዓት ታስተምራቸውና ትመክራቸው ነበር:: እነርሱ ግን ይጠሏትና ከሹመቷ የምትሻርበትን፣ ከቤተ ክርስቲያን የምትባረርበትን ምክንያትም ይፈልጉባት ነበር:: ከዚህ በኋላም በእመምኔትዋ ላይ ርኩስ መንፈስ አደረባትና ገዳሙን ከሚያገለግለው አንድ ጎልማሳ ፀነሰች:: መነኮሳዪያቱም (ከ512-538 ዓ.ም) የአንጾኪያ ኤጲስቆጶስ ከነበረው ከአባ ሳዊሮስ ዘንድ እንደ ከሰሷት ተረዳችና ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዳ በእመቤታችን ሥዕል ፊት ቆማ እየሰገደች በማሕፀኔ ያለውን ችግር አቃልሊልኝ እያለች ጸለየች:: እመቤታችንም ከማሕፀኗ ያለውን ችግር አቃለለችላት:: ነገር ግን ሕጻኑን የወተት ላሞች ላሉት ፊሊኒክስ ለሚባል ሰው ያሳድገው ዘንድ ስጡት ብላ ሁለት የብርሃን መላእክትን አዘዘች

መላእክትም የታዘዙትን ፈጸሙ:: ከእንቅልፏም ብትነቃ ምንም አይነት የፅንስ ምልክት ፈጽሞ የሌለባት መሆኑን ስትረዳ ተደሰተች:: ከሳሾቿም በቀጠሮው ቀን ቢመረምሯት የፅንስ ምልክትን አላገኙም:: ነገር ግን እመምኔቷ እመቤታችን ያደረገችላትን ተአምር ለአባ ሳዊሮስ ብቻ ነገረች:: እርሱም እጅግ ተደነቀ ሕጻኑም አደገ:: ወደገዳምም ገብቶ ተምሮ ኤጲስቆጶሱ ሳዊሮስ ከዐረፈ በኋላ በእርሱ ፈንታ ሸሙትና ባለ ዘመኑ ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግል ኖረ (297 ተአምረ ማርያም)::

፻፲:፦110 ምንተ ያሠልጥ ደመ ዚአየ እመ ወረድኩ ውስተ ሙስና፣
መሬትኑ ይነግር ዘተአምርኪ ዜና፣
ወስክኒ ሊተ ዓመተ ሕይወት ወጥዒና፣
መዓዛ ፍቅርኪ ዘይመሥጥ ኅሊና፣
እግዝእትየ ጽጌሃ ለሐና::

(7) ጠቢባን ነን የሚሉ ሰዎች ሐሳባቸው ከንቱ እንደሆነ እግዚአብሔር ያውቃል መዝ. 93.11::



የፍቅርሽ መዓዛ ኅሊናን የሚመሥጥ የሐና አበባዋ (ደስታዋ) እመቤቴ ማርያም ሆይ አባትሽ ዳዊት ሞቼ ወደ መቃብር ብወርድ የእኔ ደም ምን ግዳጅ ይፈጽምልሃል? መቃብር ሥጋውን አበላኝ፣ ደሙን አጠጣኝ ብሎ ያመሰግንሃልን? ብሎ የነቢያት ደም ሁሉ ዓለምን አለማዳኑን ለእግዚአብሔር እንደተናገረ ሁሉ መዝ.29.9 እኔ ሞቼ ወደ ጥፋት ብወርድ የእኔ ደም ምን ግዳጅ ይፈጽማል? መሬትስ የተአምርሽን ዜና ይናገራልን ሕይወት የሆነ የጤና ዘመንን ጨምሪልኝ::

፻፲፩:፦111 መኑ በመቃብር ዘይሴብሖ ለልዑል፣
ዓቢየ ትእምርት (ትምህርት) ሲራክ በከመ ይነግር ወይብል፣
ጸግውኒ ድንግል ኑኃ መዋዕል፣
ከመ እሰብሕ ተአምረኪ በማኅሌተ ጽጌ ዘኮል፣
እስመ ተነደፍኩ ለፍቅርኪ በሐፁ ስሑል::

በትንቢቱ (በመንፈሳዊ እውቀቱ) ከፍ ያለ ሲራክ ልዑል እግዚአብሔርን በመቃብር የሚያመሰግነው ማን ነው ብሎ እንደተናገረ፣ ሲራ.17.27-31፣ ድንግል ሆይ በተሳለ የፍቅርሽ ጦር ተነድፌአለሁና፣ እንደ እንኮይ ደስ በሚያሰኝና ማኅሌተ ጽጌ በተባለ ምስጋና፣ ተአምርሽን አመሰግን ዘንድ ረዥም ዕድሜን ስጭኝ::

ሲራክ .አባቱ አልዓዛር የሚባል ሲሆን፣ ትውልዱ. ከነገደ ሌዊ ነው በነቢይነት የተነሳውም ከባቢሎን ምርኮ በኋላ ነው ሲራክ ማለት ጸሐፊ (መድኃኒት) ማለት ነው (የመጽሐፈ ሲራክ መግቢያ):: ሲራክን ትንቢቱ (መንፈሳዊ እውቀቱ) ከፍ ያለ ነው ያሰኘውም ከነቢያት በኋላ ተነሥቶ ከነቢያት መዓርግ ደርሷልና ነው ሲራ 49.11::

፻፲፪:፦112 ዘያሠምረኪ ማርያም ፍሬ ጽድቅ እፍረይ አሐደ፣
ወሕየው ለኪ እንዘ እገብር ዘዚአኪ ፈቃደ፣
ለመላእክተ ሞት ዘማዕረር እለ ይፀውሩ ማዕፀደ፣
በሊዮሙ እምስብሐትየ እስከ ይጸገ ውኁደ፣
ወይነ ተአምርየ ዘንተ ኅድጉ ገሚደ::

(8) [illegible] የስማይና የምድር ፈጣሪ የሆነ እግዚአብሔር ብቻ ነው [illegible]

www.ethiopianorthodox.org

*ማርያም ሆይ ያንችን ፈቃድ እየፈጸምኩ ደስ የሚያሰኝሽ አንድ የጽድቅ ፍሬን አፍርቼ በሕይወት እኖር ዘንድ የመከር ማጭድን የሚይዙና የሞት መልእክተኞች የሆኑ አጋንንትን ከምስጋናዬ ጥቂትን እስኪያፈራ ድረስ የተአምሬ ወይን የሆነ ይህን አገልጋዬን ተዉ አትቁረጡ በያቸው::*

፻፲፫:-113 ውስተ አፀደ ወይን ዘበጋዲ ከመ ይጸጊ አስካል፤
ተአምረ ፍቅርኪ ይጽጊ በላዕሌየ ድንግል፤
ኢትመንንኒ ለኃጥእ ሤጠ ደመ ወልድኪ ቃል፤
ሰብእኒ መንኖ ንዋዩ ኢይክል፤
ዘተሣየጠ በወርቁ ዝትል::

*ድንግል ሆይ የወይን ቦታ በሆነውና ጋዲ በሚባል አገር ያለ ወይን እንደሚያብብ የፍቅርሽ ተአምር በኔ ላይ ያብብ ዘንድ ቃል የሚባል ልጅሽ ዮሐ.1.1 ከጎኑ በፈሰሰ ደሙ የገዛኝ ኃጢአተኛ የሆንኩ እኔን አትናቂኝ፣ 1ኛ ጴጥ.1.18. ሰው እንኳ በሚዝግና በሚበላሽ ወርቁ (በገንዘቡ) የገዛውን ዕቃ አይንቅም ማቴ.6.19-22::*

## የተቀበረ ወርቅ ጌታውን ስለ ማቃጠሉ

(ታሪክ) ያን ጊዜ ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት፣ ዛሬ ግን ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ በተባለው ትምህርት ቤት፣ በአክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ ተዘጋጅቶ የጠቅላይ ቤተክህነት ጽ/ቤት መጋቢት (24) ቀን (1943) ዓ.ም በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ያሳተመውና መርሐ ልቡና የተባለ መጽሐፍ፣ ዩርማኑስ እና ጳላድዮስ የሚባሉ ጸሐፍያን እንደጻፉትና ታሪኩ ዜና አበው በተባለ መጽሐፍ እንደሚገኝ፣ ፍጹም ገንዘብ ወዳጅ የሆነ አንድ ሰው ነበር ይህ ሰውም አንድ ድስት ሙሉ ወርቅ ማለትም ወርቁን (ገንዘቡን) በአንድ የሸክላ እቃ ሞልቶ ከራስጌው (ከሚተኛበት አጠገብ) ምድሩን ዝቅ አድርጎ ቆፍሮ ቀብሮ ሲኖር፣ ከዕለታት አንድ ቀን ዘመዶቹን ጠርቶ ስሞት በዚህች ላይ ራሴን አድርጋችሁ ቅበሩኝ ብሏቸው

(9) ድንጋይን በመወርወር፣ አፈርንም በመበተን ንጉሥ ዳዊትን ይረግም የነበረ እና ከንጉሥ ሳኦል ቤተዘመድ የሆነ ሳሚ የሚባለው ሰው፣ 2ኛ.ሳሙ.16.5-14፣ በኢየሩሳሌም የቁም እስረኛ ሆኖ ከኖረ በኋላ መሐላን በማፍረሱ በንጉሥ ሰሎሞን ተገደለ 1ኛ.ነገ.2.36-46::

www.ethiopianorthodox.org



ነበርና፣ ሲሞት ከዚያ ቀበሩት፣ በ3ኛው ቀንም እሳት ከመቃብሩ እየጨሰና እየነደደ ታየ ቆፍረው ቢያዩትም ወርቁ እሳት ሆኖ አቃጥሎትና ሌላ አካሉን ጨርሶ ራሱን (ጭንቅላቱን) ተያይዞት ተገኝቷል፣ ይህ ሰው ወርቁን (ገንዘቡን) ድስት በሚባል የሸክላ እቃ አኑሮ ተንተርሶት ይተኛ ነበርና፣ ባለድስት ለማለት በዓለ መቅጹት (ባለድስት) የሚል ቅጽል ስም ነበረው፣ ይህ ወርቅም በኃጢአት (በንፍገት) የተሰበሰበ ወርቅ ነበርና፣ ነዳያን ሊረዱበትና ቤተ ክርስቲያን ሊታነጽበት አይገባም ብለው ከባሕር ጥለውታልና:: እናንተ ባለጠጎች! ስለሚደርስባችሁ ጭንቅ ዋይ ዋይ እያላችሁ አልቅሱ ሀብታችሁ ተበላሽቷል፣ ልብሳችሁም በብል ተበልቷል፣ ወርቃችሁና ብራችሁም ዝጓል፣ ዝገቱም ምስክር ይሆንባቸዋል፤ ሥጋችሁንም እንደ እሳት ይበላል ብሎ ሐዋርያው ያዕቆብ የተናገረው ቃልም በዚህ ሰው ተፈጸመ ያዕ.5.2-4::

፻፲፬:-114 ለመኑ አኀዝኖ እመ ጠፋእኩ በከንቱ፣
በደመ ገቦሁ ጽጌኪ ዘተሣየጠኒ ሎቱ፣
መሐርኒ ድንግል ለመፍቀሬ ምሕረት (ለመፍቀሬ ሰብእ) ወላዲቱ፣
ምሕረትሰ ሕገ ልብኪ (ሕገ ወልድኪ) ውእቱ፣
ተአምርኪ ስምዐየ በዝንቱ (ለዝንቱ)::

*ሰውን ለሚወድ እና የምሕረት ባለቤት ለሆነ ጌታ እናቱ የሆንሽ ድንግል ሆይ ራሱን ሠውቶ ልጅሽ ከጎኑ ባፈሰሰው ደሙ ቤዛ ሆኖኝ (ኤፌ.1.7-9) እኔ በከንቱ ብጠፋ ማንን አሳዝናለሁ? ማሪኝ፤ ይቅርም በዪኝ ምሕረትስ (ይቅር ማለትስ) የልጅሽ (የልብሽ) ሕግ ነውና በዚህም (ለዚህም) ምስክሬ ተአምርሽ ነው::*

፻፲፭:-115 ኢታሕምምኒ ማርያም የአክለኒ ዘቀዲሙ፣
ለጽጌ ከርሥኪ ንጹሕ ዘዲበ መስቀል ሕማሙ፣
እመ አተከዝኩኪ አንስ በገቢረ ርስሐት ለስጌሠሙ፣
ተአምረ ምሕረት ወፍትሕ ግበሪ ዳዕሙ፣
ለዘበደምየ ተቶስሐ ለወልድኪ ደሙ::

(10) ታላላቅ መርከቦች፣ ታናሽ በሆነ መቅዘፊያ ይመራሉ፣ ፈረሶችም በልጓም ይገታሉ ያዕ.3.5-6::

*ማርያም ሆይ ልጅሽ ቀድሞ በመስቀል ላይ የተቀበለው መከራ ይበቃኛል እኔ በየቀኑ ኃጢአትን በመሥራት ባሳዝንሽ የልጅሽ ደሙ ከደሜ ስለተቀላቀለ (በደሙ ለአዳነኝ) ለእኔ የይቅርታና የፍርድ ተአምርን አድርጊልኝ እንጂ ለመከራ አሳልፈሽ አትስጭኝ::*

፻፲፮፡-116 ኀልዮ ጻዕረ ሞት ጸዋግ ያደነግጾ ለልብየ፣
ከመ ይነግር ባሕቱ ተአምርኪ ተስፋየ፣
በጺሐኪ ድንግል ጊዜ ዕረፍትየ፣
ጽጌ ዕፀ ገነት ውግሪ (ገሪ) ላዕሌየ ፣
በመዓዛሁ ትትመሠጥ ነፍስየ::

*ድንግል ሆይ ክፉ የሆነ የሞት ጻዕርን ማሰብ ልቤን ያስፈራዋልና፣ ተስፋዬ የሚሆን ተአምርሽ እንደሚናገር፣ ነፍሴ በመዓዛው ትነጠቅ ዘንድ በዕረፍቴ ጊዜ ደርሰሺ የገነት ዛፍ አበባን በላዬ ላይ ጣዪ (በገነት እኖር ዘንድ አድርጊኝ)::*

፻፲፯፡፡-117 ጽጌ ደንጎላ ዘቆላ ወእኮ ዘደደክ ፣
ዘጸገይኪ ጽጌ በማእከለ አይሁድ አሥዋክ ፣
ተአምረ ድኂን ማርያም ዘልማድኪ ምሒክ፣
መሐክኒ ለምእመንኪ እምጻዕረ ኵነኔ ድሩክ፣
ተአምኖትየ ብኪ ኢይኩን በበክ::

*የደጋ ያይደለ እንደ ቆላ የሱፍ አበባ በእሾኾች አይሁድ መካከል አበባን ያበብሽ፣ ልማድሽ ርኅራኄ የሆነ የመዳን ምልክት ማርያም ሆይ በአንቺ መታመኔ ከንቱ ሆኖ እንዳይቀር፣ ጽኑ ከሆነ የፍርድ ቅጣት ለምተማመንብሺ ለእኔ ራሪልኝ::*

*(ሐተታ) አይሁድን በግብራቸው እሾህ ይላቸዋል (ሃይማኖተ አበው እትም ምዕ. 66.23):: እመቤታችንን በእሾህ መካከል አበባን ያበብሽ ማለቱም በምድረበዳ እሾህ እየወጋት በአበባ የተመሰለ ልጇን መኃ. 2.12 ይዛ ስለ ተሰደደች ነው::*

(11) ለሰው ልጅ፣ የቃልና የንግግር መፍለቂያ፣ የሰው ስሜት (ሐሳብ) የሚገለጽበትና በአካል ትንሽ የሆነ አንደበት (ምላስ) እሳት ነው ያዕ.3.5-6::



፻፲፰፡-118 ማርያም በሊዮ ለጽጌ ከርሥኪ በሐሩረ ፀሐይ ዘመጽለወ፣
ተዘኪረከ ወልድየ ትእምርተ ንግደትየ በድወ፣
ለፍቁርየ ጸግዎ እሞተ ሲኦል ሐይወ (ሐዪወ)፣
እመሰ ለሕይወት ኢኮነ ድልወ፣
እንበዕየ ቦኑ ለከንቱ ተከዕወ::

*ማርያም ሆይ በፀሐይ ሐሩር (በፀሐይ ሙቀት) የጠወለገ የማሕጸንሽ ፍሬ ልጅሽን፣ ልጄ ሆይ በበረሃ የመኼዴን ምልክት (ወደ በረሃ መሰደዴን) ማቴ.2.13-19፣ ራእ.12.6-7 አስበህ ለወዳጄ ከሲኦል ሞት መዳንን ስጠው፣ ለሕይወት የተዘጋጀ ካልሆነ ግን ዕንባዬ በውኑ ለከንቱ ፈሰሰን? በዪው::*

፻፲፱፡-119 አድኅንኒ በተአምርኪ ዳግመ ኢያስቆቁ፣
ሰቆቃወ ዚአኪ ድንግል ይበቍዐኒ በሕቁ፣
እስመ አንቲ ወትረ መድኃኒተ አዳም ወደቂቁ፣
ኀልዪ ኃጥአነ እስከ አድኅነ በጽድቁ፣
ከመ ጽጌኪ ንጉሥ ተሰቅለ ዕራቁ::

*ድንግል ሆይ ያንች ልቅሶ በእጅጉ ይበቃኛልና ዳግመኛ እንዳላለቅስ በተአምርሽ አድኚኝ፣ አንቺ ሁልጊዜ የአዳምና የልጆቹ መድኃኒት ነሽና:: ንጉሥ ልጅሽም ኃጥአንን በቸርነቱ እስከ አዳነ ድረስ ራቁቱን እንደተሰቀለ አስቢ ማቴ 27.27-32. ጌታ፣ በዘመነ ማርቆስ መጋቢት (27) ቀን ተሰቅሎ ሞተ በ3ኛው ቀን መጋቢት (29) ቀንም ከሙታን ተለይቶ ከመቃብር ተነሣ፣ (የመጋቢት 27 እና 29 ቀን መጽሐፈ ስንክሳር)::*

፻፳፡- 120 እንበይነ አውሎጊስ ለዳንኤል አመ አርአዮ ስቅለተ፣
ከመ እገሪሁ ሰዐምኪ ወሰአልኪዮ ምሕረተ፣ .
ለተአምረ ሣህል ወልድኪ በእንተ ፍቅረ ሰብእ ዘሞተ፣
እንዘ ታዘክሪዮ ድንግል ይምሐረኒ ሊተ፣
ከናፍሪሁ ጽጌ አንኒ ስዕመተ::

*ድንግል ሆይ ስለሰው ፍቅር የሞተና የይቅርታ ባለቤት የሆነ ልጅሽን በአውሎጊስ ምክንያት ለዳንኤል መሰቀልን በአሳየው ጊዜ እግሩን እየሳምሽ (ወደ እርሱ ቀርበሽ) ምሕረትን እንደ ለመንሽው*

(12) ከሰው አንደበት፣ በረከት እና መርገም (እውነትና ሐሰት) ይወጣሉ ያዕ.3.9-13 እና ትምህርተ ኅቡኣት 32ኛው አንቀጽ (ተራ ቍጥር)::

www.ethiopianorthodox.org

*ሁሉ፤ ይምረኝ ዘንድ አበባ (ለዓለም ደስታ የሆነ) ልጅሽን አብዝተሽ ለምኚው::*

## የአውሎጊስ ነፍስና የዳንኤል ስቅለት

(ታሪክ) ከቅጠል በቀር ሌላ ሳይመገብ (40) ዓመት (ከ6) ወር በአስቄጥስ ገዳም የኖረና ስሙ ዳንኤል የሚባል አንድ መነኩሴ ነበር ድንጋይ እየወቀረና እየሸጠ ድሆችን የሚመግብና ለውሾች የሚራራ አውሎጊስ የተባለ ሰውም ነበር መነኩሴው ዳንኤልም የዚህን ሰው በጎ ሥራ አይቶ ደስ ቢለው የዚህን ዓለም ብልጽግና እንዲሰጠውና ለድሆች የሚመጸውተውን እንዲጨምርለት ጌታን ለምኖ ለአውሎጊስ ዋስ ሆነው:: አውሎጊስም የሚወቅረውን ድንጋይ ሲፈነቅል በሸክላ እቃ ውስጥ ወርቅ አገኘ ባገኘው ወርቅም ድሆችን መርዳት ትቶ የንጉሥ የሠራዊት አለቃ ሆኖ ተሾመበት:: አባ ዳንኤልም አውሎጊስ በጎ ሥራውን የተወ መሆኑን ሰምቶ ስለ አውሎጊስ ጌታን በመለመኑ ተጸጸተና ጌታ ለፍርድ እንደመጣ ሆኖ አባ ዳንኤል እንዲሰቀልና የአውሎጊስን ነፍስ ከእርሱ እንዲሹ አዘዘ:: በእርሱ (በአባ ዳንኤል) ምክንያት ጠፍቷልና:: በዚህ ጊዜ እመቤታችን ልጇን ስለ እርሱ እየሰገደች፤(እጅ እየነሳች) ስትለምነው

ሌሊት አባ ዳንኤል ራእይ አይቶ ቢነቃ ደንግጦ አውሎጊስን ወደ ቀድሞ በጎ ሥራው ይመልሰው ዘንድ በጸሎትና በምሕላ፣ ግብር ገባ (ሱባዔ ያዘ)፤ ከጌታ የታዘዘ መልአክም ተገልጾ፣ ጌታ በፍጥረቱ ላይ በሚያደርገው ፍርድ ውስጥ ለመግባት በመድፈሩ አባ ዳንኤልን ገሠጸው በዚያ ወቅትም አውሎጊስን የሾመው ንጉሥ ሞቶ ሌላ ነገሠና በአውሎጊስ ላይ በጠላትነት ተነሥቶ ገንዘቡን ሁሉ ወረሰበት፡ ሊገድለውም ሲፈልገው አውሎጊስ ነፍሱን ለማዳን ከንጉሡ ሸሽቶ ወደ አገሩ ሄደና እንደ ቀድሞው ድንጋይ እየወቀረ በጎ ሥራውን

(13) የጎርጎርዮስ ቅዳሴ ትርጒም እንደገለጸው ሆሳዕና በአርያም (አርያም ከሚባል ሰማይ የተገኘ መድኃኒት) የሚለው ቃል (22) ጊዜ መባሉ (መሆኑ)፣ ጌታ (በ22ቱ) ስነ ፍጥረት የሚመሰገን መሆኑን ለማስረዳት ነው



ጀመረ:: አባ ዳንኤልም ወደ እርሱ መጥቶ ስለ እርሱ እመቤታችን ከመሰቀል እንዳዳነችው ያየውን ራእይ ሁሉ ሲነግረው አውሎጊስ እጅግ ተደንቆ ጌታን አመሰገነ:: ትዕቢት ሰውን ከፈጣሪው ትለያለችና፣ ሲራ.10.12 አባ ዳንኤል በመጨረሻ ቢተብት፣ ትዕቢትን የማይወድ ጌታ የብሕትውናን ሥራ ወደ ሚሠራው ወደ ድንግሉ ንጉሥ ወደ አኖሬዎስ ወስዶ የንጉሡን ትሕትና አሳይቶት ከትዕቢቱ ተመለሰ:: አኖሬዎስና አባ ዳንኤልም በአንዲት ቀን አስቄጥስ በምትባል ገዳም በክብር ሲያርፉ አውሎጊስና የንጉሡ ረድዕም (አገልጋይ) በዚህች ቀን በአንድነት በክብር ዐርፈዋል (የኅዳር 16 ቀን እና የግንቦት 8 ቀን መጽሐፈ ስንክሳር)::

> ፻፳፩፦121 ይትባረክ ጽጌኪ ማርያም ለልብየ ፍቅረኪ ዘከፈሉ፣
> ወኢያርኀቀ እምኔየ ለኪዳንኪ ሣህሉ፣
> ትእምርተ ኪዳንኪ ይሁብ ለዘማውያን ተደንግሎ፣
> ሶበሰ ኪዳንኪ ምክንያተ ድኂን ኢሀሎ፣
> ፈለገ እሳት ወደይን እምአስጠመ ኵሎ::

*ማርያም ሆይ ለልቤ ፍቅርሽን ያደለውና የቃል ኪዳንሽ ይቅርታው ከኔ ያላራቀ ልጅሽ ይመስገን :: የቃል ኪዳንሽ ተአምር ለዘማውያ (ዝሙትን ለፈጸሙ) ድንግልናን ይሰጣል (ንስሓ የገቡትን እን ድንግል ያደርጋል) የመዳን ምክንያት የሆነ ቃል ኪዳንሽ ባይኖ ኖሮስ የእሳትና የመከራ ወንዝ (ገሃነም) ራእ. 14.9-12 ሁሉ ባሰጠመ ነበር::*

> ፻፳፪፦122 ሚ፡ ሠናይ ከመ ጼና ጽጌ ልሑይ፣
> በኵሉ ጊዜ ምሒረ ነዳይ ፣
> በእንተ ኪዳንኪ ድንግል ለበላዔ ሰብእ ጊጉይ፣
> ሶበ ዐብየ እምኃጢአቱ ክበደ መድሎቱ ለማይ፣
> ለተአምርኪ በሰማይ ተገብረ ግናይ::

*ድንግል ሆይ ሁል ጊዜ ለደሃ መራራትና መመጽወት ደ እንደሚያሰኝ እንደ አበባ መዓዛ ምንኛ መልካም ነው? ሆሴ ፩.፮-7፤*

(14) እጁን ክፉ ከማድረግ የሚጠብቅ እና በቃሉ የማይሰናከል (አንደበቱን የሚገታ) ሰ ብፁዕ (የተመሰገነ) ነው ኢሳ.56.1-3፤ ያዕ.3.2-3::

www.ethiopianorthodox.org

*ማቴ. 9.13-14. በቃል ኪዳንሽ ምክንያት ከበላዔ ሰብእ (ሰውን ከሚበላ ስምዖን ከሚባል ሰው) ኃጢአት ይልቅ የውሃው ሚዛን ክብደት በልጦ በመታየቱ ለተአምርሽ በሰማይ ምስጋና ተደረገ፡፡*

## በእመቤታችን ቃል ኪዳን፣ ስምዖን ስለመዳኑ

(ታሪክ) አንድ ልጅ ብቻ የነበረውና ስሙ ስምዖን የሚባል አንድ ሰው ነበር እንደ አብርሃም በመልካም ሥራ ጸንቶ ሲኖር ዲያብሎስ ቀንቶበት በእንግዳ ተመስሎ ከቤቱ ገብቶ ልጅህን ሠዋልኝ (እረድልኝ) ብሎ ልጁን አሳርዶ አባት የልጁን ሥጋ እንዲበላ አደረገ ይህ ሰውም ልጁን ከበላባት ከዚያች ቀን ጀምሮ ስሙ በላዔ ሰብእ (ሰውን የሚበላ) ተባለ የዚህ ሰው ፍላጎትም የሰው ሥጋን መብላት ብቻ ሆኖ (78) ሰዎችን በላ ከብዙ ጊዜ በኋላም በመንገድ ውሃ የተጠማ አንድ ደሃ ሰው በእመቤታችን ስም ውሃ ስጠኝ ብሎ ለመነው በእውነት

አሁን የጠራሃትን እመቤት ከሕጻንነቴ ጀምሬ ባማላጅነቷ የምታድን መሆኗን አውቃለሁ ብሎ ትንሽ ውሃ በእጁ ላይ አፈሰሰለትና ጠጣ ውሃውም ለተጠማው ሰው የጉሮሮ እርጥበት እንጂ ከውሃ ጥማቱ አላረካውም ከዚህ በኋላ ግን የበላዔ ሰብእ የቀድሞ አእምሮው ተመለሰለትና ከዋሻ ገብቶ ስለበደሉ እያለቀሰና ሰውነቱን በረሀብና በጽምዕ እየቀጣ ምንም ነገር ሳይቀምስ በእግዚአብሔር ኃይል ያለ እህል ውሃ (21) ቀን ተቀምጦ ንስሓ ገብቶ ሞተ፣ አጋንንትም ነፍሱን ወደ ሲኦል ይወስዷት ዘንድ ከበቧት እመቤታችንም ልጇን ስምሽን የጠራ፣ ዝክርሽን የዘከረ እምርልሻለሁ አላልከኝምን ስትለው ጌታም ይህቺን ነፍስ ይቅር ብሏት በእመቤታችን አማላጅነት ከሲኦል ወደ ገነት ለመግባት በቃች (206 ተአምረ ማርያም)፡፡

፻፳፫፦123 ምንተኑ ለጽጌ ከርሥኪ አዐሥዮ፣
እንበይነ ኪዳንኪ ድንግል ምክንያተ ድኂን ዘወሀበንዮ፣
ባሕቱ ምስሌኪ ማርያም መጠነ ተክህለኒ አዐብዮ፣
ትእምርተ ፍሥሓየ በእንቲአኪ ዘኢይፌጽም ኀልዮ፣
ሰይጣንሰ ይበኪ ርእዮ፡፡

(15) ከነቤተሰቡ ሊሞት የነበረ ንጉሥ አቤሜሌክ፣ በአብርሃም ጸሎት (አማላጅነት) ከመቀሠፍ ዳነ ዘፍ.20.1-18፡፡



*ድንግል ማርያም ሆይ የመዳን ምክንያት አድርጎ ስለሰጠኝ ቃል ኪዳንሽ የማሕፀንሽ ፍሬ ለሆነ ጌታ ምን ዋጋን እከፍለዋለሁ፡፡ ነገ ግን በተቻለኝ መጠን ከፍ ከፍ አደርገዋለሁ፡፡ ልጅሽ በአንቺ ምክንያት ያደረገልኝ የደስታዬን ተአምር በማሰብ የማይፈጽም ሰይጣን ግ አይቶ ያለቅሳል፡፡*

## መብራትን አጥፍቶ ሲገረፍ ስላለቀሰ ሰይጣን

(ታሪኩ)፡- በመጽሐፈ መነኮሳት እንደሚገኝ፣ በገዳም አገልግሎት ጸንተው የሚኖሩ ሁለት ወንድማማቾች ነበሩ ታላቁ ታና ወንድሙን መጽሐፍ የምደግምበት (የማነብበት) መብራት አምጣልኝ ብሎት መብራት ሲያመጣለት ሰይጣን ከመንገድ ጠብቆ መብራቱ አጠፋበት ያን ጊዜ ታላቁ ታናሽ ወንድሙን ይህ ልል (ፈዛዛ) ብሉ በጥፊ መታው በዚህ ጊዜ ታናሹ ታግሦ እኔ እንዳጠፋሁት እ አመጣለሁ ሲል ጌታ የታናሹን ትዕግሥት አይቶ ከጌታ የታዘ መልአክ ሰይጣኑን በእሳት አለንጋ ሲገርፈው አደረ ሰይጣንም አይነክ ሲነኩ ያድሯል ሲታወኩ እያለ ሲያለቅስ አድሯል ስለዚህ ሰይጣ ያለቅሳል አለ፡፡

፻፳፬፦124 ውስተ ጽንፈ ልብሱ እስራኤል ትእምርተ ይኩኖ፣
በከመ ገብረ ዘፈረ እምፈትለ ጽጌ ዘኀብረ ደርከኖ፣
ግበሪ ሊተ ማርያም ትእምርተ አድኅኖ፣
ወአመስቅሊ በፍጽምየ ዋካ ዕንቍኪ ስርዲኖ፣
ለመልአከ ሞት ጸዋግ ዘይደጕጽ ዓይኖ፡፡

*ማርያም ሆይ እስራኤል በልብሱ ጫፍ ላይ ምልክትን ይሆነው ዘን ቀይና ሰማያዊ መልክ ካለው የአበባ ሐር ፈትልን በልብሱ ዘር (በልብሱ ጫፍ) እንደ አደረገ ሁሉ ዘኍ. 15.37-41. የማዳ ምልክትን አድርጊልኝ፣ የሞት መልእክተኛ (የዲያብሎስ ምሳሌ የሆነ የክፉ አውሬ ዓይኑን የሚወጋና የሚያበራ ሰርዲኖ የተባ ዕንቍሽን ራእ.4.3 በፊቴ ላይ መስቀለኛ አድርጊ (በመስቀል ምልክ ሣዪብኝ) ፡፡*

(16) በተወለደ (በ39) ዓመቱ ሊሞት የነበረ ንጉሥ ሕዝቅያስ፣ ወደ ፈጣሪ ቢጸልይ ቢያስጸልይ እግዚአብሔር (15) ዓመት ጨምሮለት ምናሴን ወልዶ (በ54) ዓመቱ ዐረ 2ኛ ነገ 20.1-21፤ ኢሳ.38.1-10፡፡

www.ethiopianorthodox.org

## እስራኤል በልብሳቸው ጫፍ ስለ አደረጉት ምልክት

ጌታ ለእስራኤል ልጆች ሥርዓት ይሆናቸው ዘንድ በልብሳቸው ዘርፍ (ጫፍ ላይ) ሰማያዊ ሕግ ሠራሁላችሁ ለማለት ሰማያዊ መልክ ያለው ፈትልን እንዲያደርጉ ለሙሴ የነገረው ሲሆን፣ ይህ ሥርዓት የተፈጸመውም ዓለም በተፈጠረ (በ3845) ዓመት በሙሴ አማካኝነት ነው ዘኁ.15.37::

## የአውሬ ዓይኑን የሚወጋ ዕንቍሽን ሣዪብኝ ለምን አለ?

(ታሪክ) ሲዶና በሚባል አገር የሚኖር አንድ ሰው ከዕለታት አንድ ቀን አውሬ ለማደን ወደ ዱር ሲሄድ አንድ ዘንዶ ዓይኑን አፍጥጦ መጣበት፣ በዚህ ጊዜ ይህ ሰው እመቤቴ ማርያም ሆይ የዲያብሎስ መልእክተኛ ከሆነ ከዚህ ዘንዶ ዘፍ.3.1.ብታድኚኝና ለንስሓ ብታበቂኝ በስምሽ ቤተክርስቲያን እሠራለሁ ብሎ በመማጸን በያዘው ጦር ዘንዶውን ወግቶ ከገደለ በኋላ ከዘንዶው ናላ (ጭንቅላት) ውስጥ የሚያበራ ዕንቍን አገኘ፣ ይህ ሰውም እጅግ ተደስቶ ቀድሞ እንደተማጸነ (ቃል እንደገባ) በእመቤታችን ስም ቤተክርስቲያን ከአሠራ በኋላ ዕንቍው የተገኘው በማርያም ተአምር ነውና፣ ለቤተክርስቲያኒቱ ይገባል ብሎ ዕንቍውን በቤተክርስቲያኒቱ ጉልላት ላይ እንደ መስቀል አደረገው:: ይህ ዕንቍም ቂሮስና ሲዶና በሚባሉ አገሮች ላይ ሲያበራ ኖረ:: (በ1989 ዓ.ም በትንሣኤ ዘጉባኤ የታተመ እና 111 ተአምራትን የያዘ 63ኛ ተአምረ ማርያም)::

ጀጽጅ፦125 ቡሩካን አርጋብ እለ በታሕቴኪ ያጸልሉ፣
ወይሴሰዩ ፍሬኪ እንዘ በደሙ ያጠልሉ፣
ዕፀ መዓዛ ማርያም ለመስቀል ትእምርተ አምሳሉ፣
እስመ ጽጌኪ ጽጌሁ ወአስካልኪ አስካሉ፣
ለክልኤክሙ ሰጊድ ይደሉ::

*የመስቀል ምልክት (ምሳሌ) የሆንሽ ዕፀ መዓዛ ማርያም ሆይ*

(17) ከወርቅ እና ከብር ይልቅ፣ የእግዚአብሔር ሕግ፣ መዝ. 93.11፣ ጥበብ፣ ኢዮ.28.12-20፣ እምነት ይሻላሉ 1ኛ.ጴጥ.1.3-10::



*በረድኤትሽ ጥላ ስር የሚጠለሉና በደሙ እያራሱ ፍሬሽን የሚመገቡ ርግቦች (ምእመናን) ቡሩካን ናቸው አበባሽ አበባው፣ ፍሬሽም ፍሬው ነውና (ጌታ ሥጋሽን ለብሶ፣ በመስቀል ተሰቅሎ አድኖናልና)፣ ለሁለታችሁ (ለአንቺና ለመስቀል) የጸጋ ስግደት ይገባል::*

(ሐተታ) ዕፀ መዓዛ የሚባለው ዕንጨት ምን አይነት ነው ቢሉ፣ ጌታ ወደ ፊት በመስቀል ላይ ሊሠራ የፈቀደውን ምሥጢር፣ ለነቢዩ ኤርምያስ በራእይ ተገልጾ፣ ኤርምያስ ሆይ ምን ታያለህ ሲለው ኤርምያስም፣ የለውዝ ዕንጨትን አያለሁ ያለው፣ በወርድ ስፋቱም (በአግድሞቱ) መስቀል የሚመስልና፣ በሌላው ዓለም የሚገኝ ለውዝ የሚባለው ዕንጨት ሲሆን፣ በሀገራችን ደግሞ፣ ሎሚ የሚባለው ዕንጨት ነው ኤር.1.10-13:: የለውዝንና የሎሚን ዕንጨት ምንነት መጽሐፍ፣ በትረ ከርካዕ ውእቱ ዕፀመስቀል፣ ወበትረ ለውዝ (ዕፀ ለውዝ) ይትሜሰል በግደሚሁ (በግዳሜሁ)፣ "የሎሚ ብትር የመስቀል ዕንጨት ነው፣ የለውዝ ዕንጨትም በአግድሞቱ (በወርድ ስፋቱ) መስቀልን ይመስላል፣ (ጌታ በተሰቀለበት የመስቀል ዕንጨት ይመስላል)" በማለት ገልጾታል:: የኪዳነወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ገጽ 302 እና መጽሐፈ ምሥጢር ምዕ.14 ቍ.25-30:: ይህም ይታወቅ ዘንድ ሕማማተ መስቀል የተባለ መጽሐፍ እንደተናገረው ጌታ፣ ከተሰቀለባቸው ከ8 (ከ7) ዕፀዋት መካከል፣የዘይትና የወይራ ዕንጨቶች ይገኙበታል:: መስቀልም በነዚህ ዕፀዋት፣ ማለትም፦

1ኛ. የውጭ አካሉ እና (ቆዳው እና) የውስጥ ፍሬው፣ እጅ ጣፋጭና መድኃኒት በሆነው በለውዝ ዕንጨት የመመሰለ ምሥጢር፣ ጌታ በመስቀል ላይ የቆረሰውንና ያፈሰሰው ሥጋና ደም፣ በንስሐ ለተቀበለው ሰው የነፍስና የሥ ሕይወት ነውና::

2ኛ. ልዩ መዓዛ በአለው በሎሚ ዕንጨት የመመሰሉ ምሥጢር የጌታ ምሳሌ ከሆኑ ከመልከጼዴቅ እና ከአሮን ክህነት ይልቅ፣

(18) ተስፋ፣በዚህ ዓለም የማይታይ ሲሆን በሚመጣው ዓለም (በመንግሥተ ሰማያ የተረጋገጠ የማይጠፋ ሰማያዊ ሀብት ነው ዕብ.11.1-4::

www.ethiopianorthodox.org

መዓዛ ክህነቱ እጅግ የተወደደ ኢየሱስ ክርስቶስ መዝ.109.4፣ ዕብ.5.1-11፣7.1-4. ያለ ውሃ ለምልማና አፍርታ ለተገኘች ብትር ዘኍ.17.6-10 ምሳሌ ከሆነች ከድንግል ማርያም፣ ያለዘር የነሣውን ሥጋና ደም ፣ ማቴ.1.18-24. በዚህ ዕንጨት ላይ ሰቅሏልና::

3ኛ. ከእርሱ የሚገኘው ቅባት፣ ለመብራት በሚሆነው በዘይት ዕንጨት የመመሰሉ ምሥጢር፣ መስቀል ለዓለም ሁሉ ብርሃን ነውና::

4ኛ. እንደዚሁ እጅግ ጠንካራ (ብርቱ)፣ ቅባቱም መድኃኒት በሆነው በወይራ ዕንጨት የመመሰሉ ምሥጢር፣ ምእመናን መስቀል ኃይላችን፣ መስቀል መድኃኒታችን ነው እያሉ ይመኩበታልና ነው 1ኛ.ቆሮ.1.18-19::

ሀ፳፮፦126 ዝንቱ መስቀል መንበረ ነበልባል ዘኪሩቤል ቢጽ፣
አምሳለ ስምኪ ድንግል ርቡዕ ሆህያት ወገጽ፣
ለእለ ተውህበነ ትእምርት በዘናመሥጥ እምሐፅ፣
አውኅዘ ደመ ወማየ በኢየሩሳሌም ወግብፅ፣
ዘውእቱ ስቴነ ወሰዋቂነ እምዳሕፅ፣
ደመ (ወይነ) መለኮት መደንግጽ ጽጌሁ ለዕፅ::

*ድንግል ሆይ እንደ ስምሽ በመልክና በፊደል አራትነት ያለው፣ የኪሩቤል ጓደኛ (አምሳያ) የተባለ ይህ የነበልባል (የመለኮት) ዙፋን የሆነ መስቀል፣ ከጦር (ከሰይጣን ፈተና) እንድንበት ዘንድ ምልክት ለተሰጠን ለእኛ በኢየሩሳሌምና በግብፅ ደምንና ውሃን አፈለቀልን፣ ይኸውም መጠጣችንና ከዳጥ ደጋፊያችን ከሚሆን ከዛፍ ፍሬ (ጳጦስ በምትባል ዕንጨት ከተመሰለች ከድንግል ማርያም ዘጸ.3.2-5) የተገኘ የሚያስደነግጥ የመለኮት ደም ነው::*

(ሐተታ) መስቀልን የኪሩቤል ጓደኛ ነው ማለቱ፣ ኪሩቤል የሚለው የፊደል ቍጥርና የኪሩቤል ፊታቸው (4) እንደሆነ ሁሉ ሕዝ 1.5-25፣

(19) የእግዚአብሔር ጸጋ (ስጦታ) የሆነው ተስፋ፣ ሮሜ.15.13-14፣ ምኞትና ናፍቆት ብቻ (ከንቱ) ሆኖ የማይቀር ሰማያዊ የክርስቲያን መሠረት ነው 1ኛ.ቆሮ.15፡9-11::



ራእ. 4.6-9 መስቀል የሚለው የፊደል ቍጥርም (4) ስለሆነ ነው
እመቤታችንን እንደ ስምሽ የመስቀል ፊደሉ (4) ነው ያለው ደግሞ፣
ማርያም የሚለው ፊደል እንደዚሁ እንደ ኪሩቤልና እንደ መስቀል
(4) መሆኑን የሚገልጽ ሲሆን፣ 4ቱ ኪሩቤልም (4ቱ መላእክትም
መንበሩን እንዲሸከሙ መስቀል በዕለተ ዓርብ ጌታን ከቀኑ (6) ሰዓት
ጀምሮ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ የሚባሉ ሁለት ሰዎች ከመስቀሉ
እስከአወረዱበት እስከ (11) ሰዓት ድረስ (ከ4) ሰዓት በላይ ተሸክሞ
መዋሉን የሚያነጻጽርና የረቀቀ ምሥጢርን አጉልቶ የሚያስረዳ ነወ
ማቴ 27.27-46:: መስቀል፣ በኢየሩሳሌም እና በግብፅ ደምንና ውሃ
አፈለቀልን ማለቱም፣ ጌታ እንደ ገሊላ ሕጻናት በሕጻንነቱ
(ያለጊዜው) ደሙ እንዳይፈስስ በአምላክነቱ ባሕርይ አውቆና ወ
ግብፅ ተሰዶ ያቆየውን ሕይወት፣ ደሙን አፍስሶ ዓለምን ለማዳ
ጊዜው ሲደርስ በኢየሩሳሌም ተሰቅሎ ነፍሱን ከሥጋው በገ
ሥልጣኑ ከለየ ከሁለት ሰዓት በኋላ፣ አንድ ዓይና የነበረ እና ስመ
ለንጊኖስ የሚባል ሰው፣ ቀኝ ጎኑን በጦር ቢወጋው፣ ሥጋው ገ
በመስቀሉ ላይ እያለ ለጥምቀታችን የሚሆን ጥሩ ውሃ፣ ለቍርባናች
የሚሆን ትኩስ ደም አንድነት ወጥቶ እንደ (ለ) ፊደል መንታ ሆ
ፈስሶ ነበርና ነው (ዮሐ.19.31-36 እና ሕማማተ መስቀል አማርኛ)::

የመለኮት ደም የሚያስደነግጥ ነው ማለቱም፡-

1ኛ. የጌታ ሥጋውንና ደሙን ከኃጢአት ሳይነጹ ቢቀበሉት ፍ
ያመጣልና ነው 1ኛ.ቆሮ.11.27. ሰው ከሞተ በኋላም ቢወጉ
ትኩስ ደም አይወጣውም፣ ውሃም ፈጽሞ አይወጣውም:: ጌ
ግን ታሪኩ ቀደም ሲል እንደተገለጸውና እንደተመለከትነ
ነፍሱ ከሥጋው ከተለየች ከሁለት ሰዓት በኋላ፣ ለጥምቀታች
የሚሆን ጥሩ ውሃን፣ ለቍርባናችን የሚሆን ትኩስ ደም
አስገኝቷልና ነው::

(20) አዳምና ሔዋን፣ ከገነት ሲወጡ እንስሳት፣ አራዊት፣ አዕዋፍ ምን አሉ? ⟶

www.ethiopianorthodox.org

2ኛ. ለንጊኖስ የተባለው ሰው በጦር ሲወጋው፣ ደሙ ተፈንጥቆ ከታወረች ዓይኑ ላይ ሲያርፍ እና ዓይኑ ስትፈወስ ያዩ አይሁድ፣ ከሞተ ሰው እንዴት ደምና ውሃ ሊወጣ ቻለ? እንዴትስ ደሙ ዓይን ሊያበራ ቻለ? እያሉ ደንግጠዋልና:: ማለትም ነፍስ ከተለየችው ሥጋ፣ ሕይወትነት ያለው ደም፣ መገኘቱም ሰይጣንን እና እሱ ያደረባቸው አይሁድን አስደንግጧልና ነው::

3ኛ. እንደዚሁ አምነው ሥጋውንና ደሙን ያልተቀበሉትን ሁሉ ዲያብሎስ በሲኦል ሲያስደነግጥ ይኖራልና ነው::

ጀ፳፯፡-127 ተአምረ ልደት ወጥምቀት ከሠትኪ ማርያም፣
በአውሕዞ ዘይት ወሜሮን እምአጥባተ ሥዕልኪ ዘቀለም፣
እስመ ብኪ ሀሎ ኃይለ ጽጌኪ ግሩም፣
ዘአንቅዐ ማየ ለጽምዕኪ ከመ ለሕዝቡ አንቅዐ በገዳም፣
እምኰኵሕ ልሙፅ ወይቡስ ዓፅም::

*ማርያም ሆይ በቀለም ተአምር ከተሣለ ከሥዕል ጡትሽ ዘይትንና ሜሮንን በማፍሰስ (በመንፈስ ቅዱስ) ሁለተኛ የመወለድንና የመጠመቅን ተአምር ገለጽሽ፣ ዮሐ.3.3-5:: ለወገኖቹ ለእስራኤል በበረሃ ከጭንጫ (ከልሙጥ) ድንጋይና ከደረቅ አጥንት ውሃን እንዳፈለቀ፤ ለውኃ ጥማትሽ ውኃን ያመነጨ የሚያስደንቅ የልጅሽ ተአምር ባንች አለና::*

(ታሪኩ)፡- እስራኤል ከግብፅ ከወጡ በኋላ ጌታ በሙሴ አማካኝነት ከድንጋይ ያፈለቀላቸውን ውኃና ዘጸ. 17.5-7፣ ዘኁ.20. 9-12. ሶምሶን በአህያ መንጋጋ አንድ ሺህ ሰዎችን ከገደለ በኋላ ከመንጋጋው (በመንጋጋው አማካኝነት) ውኃ ፈልቆለት የጠጣውን የውኃ ታሪክ መሳ. 15.15-20. በስደቷ ጊዜ (ሰኔ 8 ቀን) ለእመቤታችን ያፈለቀላትን ውኃ የሚያነጻጽር ነው::

---

(21) እንስሳት፣ አራዊት፣ አዕዋፍ አዳምና ሔዋን ከገነት እንደወጡ ሁሉ፣ እነሱም ከገነት የሚወጡ መሆኑን አውቀው፣ የገነት መኳንንት አዳምና ሔዋን ሆይ ከገነት ማን አስወጣችሁ እያሉ አልቅሰዋል ኩፋ.5.3-5 እና የዓርብ መጽሐፈ አክሲማሮስ ክፍል አራት::



## ሐዋርያትና በሲኦል የነበሩ ነፍሳት መቼ ተጠምቀው ነው! ሥጋውንና ደሙን የተቀበሉ?

ጌታ፣ (በ33) ዓ.ም የጸሎተ ሐሙስ (መጋቢት 26 ቀን) ከምሽቱ አንድ ሰዓት ላይ፣ ሞቶ በተነሣውና በጌታ ፈቃድ የእግር መታጠቢያ የሚሆን ውኃን በአዘጋጀው በአልዓዛር ቤት የሐዋርያትን እግር በአጠበ ጊዜ ለበረከት ከአመጡለት ኅብስትና ወይን ከፍሎ ከትንሣኤው በኋላ ሊያስተምር የፈቀደውንና ቅዳሴ እግዚእ የተባለውን የቅዳሴ ምስጋና በኋሊና ደግሞ፣ ነገ በመስቀል ላይ ለዓለም ቤዛ ሊሆን የሚሰቀል ሥጋዬ እና የሚፈስስ ደሜ ይህ ነውና፣ እንኩ ብሉ፣ ጠጡም ብሎ ቀድሞ የበሉትንና የጠጡትን በአምላካዊ ግብር (በአምላካዊ ጥበብ)፣ ከሆዳቸው አጥፍቶላቸው አክብሮና ለውጦ ሰጣቸው:: (ማቴ.26.20-30 እና ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ ምዕ.2.ቍ.40-43. ንባቡና ትርጓሜው):: ከዚሁ ምሥጢር ጋር በተያያዘም ጌታ፣ የጸሎተ ሐሙስን ሥርዓት የፈጸመ በአልዓዛር ቤት፣ በስምዖን ቤት፣ በኒቆዲሞስ ቤት ነው የሚል ታሪክ ቢኖርም፣ ልዩነት የለውም:: ምክንያቱም አልዓዛር፣ ስምዖን፣ ኒቆዲሞስ (እኒህ ሦስቱ) የአንድ ሰው ልጆች (ወንድማማቾች) ናቸውና:: ወደ ጥንተ ነገራችን እንመለስና "ሐዋርያት የጥምቀት መሥራች በሆነው ጌታ እግራቸውን መታጠባቸው፣ የጥምቀት ምሳሌ ሆኖላቸው ሥጋውንና ደሙን ተቀበሉ:: ማስረጃውም ጌታ፣ በጸሎተ ሐሙስ ጊዜ (መጋቢት 26 ቀን ማታ) እግራቸውን ከአጠበ በኋላ ሥጋውንና ደሙን መስጠቱ ነው:: (እግራቸውን የታጠቡ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ሲሆን፣ ሥጋውንና ደሙን የተቀበሉ ደግሞ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ነውና):: (ዮሐ.13.9-18 እና መጽሐፈ ምሥጢር ምዕ.14.21):: በተመሳሳይ ምሥጢርም፣ ለ5,533 ዘመን ያህል በሲኦል የነበሩ ነፍሳት ሁሉ፣ ያልተጠመቁ እና ያልቈረቡ ቢሆኑም፣ ያለ ጥምቀት፣ ያለ ሥጋውና

---

(22) ጌታ፣ በዕንጨት ለምን ተሰቀለ? በእርጥብ ዕንጨት መሰቀሉስ ስለምንድነው?

www.ethiopianorthodox.org

ያለ ደሙ፣ ጽድቅ አይገኝምና፣ ዮሐ.3.3-8፤6.47-57. ጌታ፣ በዕለተ ዓርብ በአካለ ሥጋው ተሰቅሎ ሳለ በአካለ ነፍሱ ሲኦል ወርዶ፣ የተወጋ ቀኝ እጁን ቢያሳያቸው፣ ከጐኑ የፈሰሰው ደም እንደ ጥምቀትና እንደ ቊርባን ሆኖላቸው ገነት ገብተዋል። ሥጋውንና ደሙን ስንቀበልም፣ ይህ ሥጋና ደም ነፍስ የተለየው፣ መለኮት የተዋሐደው ነው ብለን በማመን ነው (ሕማማተ መስቀል አማርኛ)።

## ከሥዕል ጡቶች የፈለቀው ዘይትና ሜሮን

(ታሪክ) ከነገደ እስራኤል ወገን የሆነ፣ ያልተጠመቀና በዓረብ አገር የሚኖር አንድ ሰው ነበር ከዕለታት አንድ ቀን በቤቱ ውስጥ ተቀምጦ እንዳለ ከየት እንደመጣች ያላወቃት የእመቤታችንን ሥዕል አገኘ ደስም አለችውና በዚህች ሥዕል ፊት ቆሞ ሳለ ከሥዕሏ ደረት ላይ ካሉ ሁለት ጡቶች ዘይትና ሜሮን ሲንጠባጠብ አየ። የሥዕሏም ሁለንተናዋ ሥጋን የለበሰ ሰውን ትመስላለች ይህ ሰውም ይህን ድንቅ ተአምር አይቶና አምኖ ከነቤተሰቡ ተጠምቆ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ እመቤታችንን ሲያገለግል ኖረ (239 ተአምረ ማርያም)።

## ጥምቀት ወደ ኢትዮጵያ እንዴትና መቼ መጣች?

(ታሪክ) አማናዊት ጥምቀት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ተጀመረች (ማቴ.3.11.) ወደ ኢትዮጵያስ የመጣች መቼና በማን ነው ቢሉ! በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ አማካኝነት ነው ይህ ጃንደረባም ከአባቱ ከዕብነ መልአክና ከእናቱ ከሥነ ሕይወት (በ01 ዓ.ም) ታኅሣሥ (29) ቀን ተወለደ መጠሪያ ስሙም አቢላክ (ባኮስ) ይባላል። ስለ ጃንደረባነቱም (ስለ ስልብነቱም) ታሪኩ እንደሚያስረዳ ጌታ ስለ መንግሥተ ሰማያት ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ ብሎ እንደተናገረ (ማቴ.19.10-13.) ራሱን በፈቃዱ ጃንደረባ ያደረገና ሙሉ ዕድሜውን በድንግልና ያሳለፈ ሃይማኖተኛ ሰው ነበር፤ ይህ

(23) ጌታ፣በዕንጨት የተሰቀለበት እና ዕንጨቱ እርጥብ የመሆኑ ምሥጢር፣ በሰመለመች ዕንጨት (በዕፀ በለስ) ምክንያት፣ የመጣች ኃጢአትን ለማጥፋትና የሰመለመች የዕንጨት ፍሬን በልተው ከገነት የወጡ አዳምና ሔዋንን ለማዳን በእርጥብ ዕንጨት ተሰቀለ ዘፍ.3.6-24 እና ሉቃ.23.26-39።



ሰውም መጠሪያ ስሟ ጌርሳሞት፤ የንግሥትነት ስሟ ደግሞ ህንደኬ (ሕቴጌ) ለተባለች ለኢትዮጵያ ንግሥት ታማኝና ከፍተኛ ባለሥልጣ (ገንዘብ ሚኒስቴር) ነበር። በተወለደ (በ34) ዓመቱ እንደተለመደው በየዓመቱ የኦሪቱን ሥርዓት ለማክበር ኢየሩሳሌም ሄዶ የአምል ሥርዓቱን ፈጽሞ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለስ፣ የጌታ መልአክ እን ነገረው ወንጌላዊው ፊልጶስ፣ ጃንደረባውን በሰረገላ ተቀምጦ እግዚአብሔር የሁላችንን በደል ተሸከመ፣ እንደበግ ወደመታረድያ ተነዳ፣ ተሰቃየ፤ አፉንም አልከፈተም የሚለውን የነቢዩ የኢሳይያስን መጽሐፍ ሲያነብ አገኘውና ኢሳ.53.6-10. ያልተረዳውን ቃ ተርጉሞ አስረዳው፣ ጃንደረባውም በጠየቀው መሠረት ሳሮን (ሶሮን ከሚባል ወንዝ ጥግ ከምትገኝ ከአንዲት ምንጭ ውሃ ደረሱ አጠመቀው (የሐዋ. ሥራ.8.26-40)። የተጠመቀም ኅዳር (18) ረቡ ከቀኑ (6) ሰዓት ነበር ከተጠመቀ በኋላም ምድራዊ ሥልጣኑን በፈቃዱ ለቆ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይወሰን ወደተለያዩ ዓለማ እየተዘዋወረ (ለ41) ዓመታት ያህል ወንጌልን ሲያስተምር ኖ በተወለደ (በ75) ዓመቱ ጥር (18) ቀን ሲሉን በምትባል አገ (በዛሬዪቱ ታይላንድ) በሰማዕትነት ዐረፈ። ቅዱስ ያሬድ በዐረፈበ በኢትዮጵያ ሰሜን ተራራ ዐርፏል የሚሉ ሊቃውንትም አሉ (የቅዱሳን ታሪክ በሊቀ ብርሃናት መርቆሬዎስ አረጋ 1998 ዓ.ም እና የተለያ የታሪክ መጻሕፍት)።

ጀጀጀ፦128 ናሁ እምላዕሌየ ክረምተ ኀዘን ኀለፈ፣
ወጽጌ ስብሐትኪ ትፍሥሕት ውስተ ልብየ ሰፈፈ፣
እምነ ሥዕልኪ ድንግል ከመ ታውኀዚ ሐፈ፣
ዘሰማዕኩ በጼዴንያ ተአምረኪ ጽሑፈ፣
በኢትዮጵያ ርኢኩ ትሩፈ።

*ንጉሥ ሰሎሞን ክረምቱ አልፏልና መልካሟ ርግቤ ሆይ ነዪ ብ እንደተናገረ መኃ.2.11. እነሆ ከእኔ ላይ የኀዘን ክረምት አለፈ፣ ደስ*

(24) ጌታ፣ ዓርብ ከቀኑ (6) እስከ (9) ሰዓት በመስቀል ላይ ውሎ (በ9) ሰዓት ነፍሱን የለየበ ምክንያት፤ አዳምና ሔዋን ዕፀ በለስን የበሉ ዓርብ ከቀኑ (6) ሰዓት ሲሆን፣ ከገነትም የወ (በ9) ሰዓት ነበርና፣ በዚሁ ሰዓት እነሱን ወደ ገነት ለመመለስ ነው (የዓርብ መጽሐ አክሲማሮስ ክፍል አራት)።

www.ethiopianorthodox.org

*የሚያሰኝ ምስጋናም በልቤ ውስጥ ሞላ ድንግል ሆይ ከሥዕልሽ ወዝን እንደ ምታፈልቂና ጼዴንያ በምትባል አገር ተጽፎ የሰማሁት ተአምርሽን በኢትዮጵያ ምልቶና ተትረፍርፎ አየሁ::*

## የእመቤታችን ሥዕል በጼዴንያ ድምጽ ማሰማት

(ታሪክ) ጼዴንያ በምትባል አገር የከበረችና የተመረጠች ማርታ የምትባል አንዲት ሴት ነበረች የእንግዳ መቀበያ ቤትን ሠርታ እንግዶችን መቀበል አዘወተረች በዚህም መሠረት በቤቷ ከአደሩት እንግዶች አንዱ የሆነ አባ ቴዎድሮስ የሚባለው ኢትዮጵያዊ ወንጌላዊ ሉቃስ የሣላትን የእመቤታችንን ሥዕል ከኢየሩሳሌም እንዲያመጣላት ቃል ገባ ሲመለስ ግን አንበሳ እና ወንበዴዎች ሲመጡበት ሥዕሏ ከፍተኛ ድምፅ ስታሰማ ሰምቶ፣ አንበሳውና ወንበዴዎችም ሲሸሹ አይቶ፣ ሥዕሏ ከአደረገችለት ተአምር የተነሣ ሥዕሏን ወዶ፣ መንገድ ለውጦ በሌላ መንገድ ሲሄድ በመርከብ ውስጥ ዓውሎ ነፋስ ተነሣና ያለ ፈቃዱ ወደ ጼዴንያ ተመልሶ ከማርታ ቤት አድሮ እሄዳለሁ ሲል መሄድ ተስኖት በ3ተኛው ቀን ተጸጽቶ በመንገድ ያየውን ሁሉ ተአምር ለማርታ ሲነግራት ማርታ በሥዕሏ ፊት ሰገደች፣ ሥዕሏም ሥጋን የለበሰች ትመስል ነበር (የመስከረም 10 ቀን መጽሐፈ ስንክሳርና 99 ተአምረ ማርያም)::

ጀ፳፱:-129 ሥዕልኪ ማርያም ጸገየት ሥጋዌ፣
ከመ ዕፀ ገነት ትጸጊ ጽጌያተ ለሥርጋዌ፣
ሣህለ ተአምርኪ እኩን ለትውልደ ትውልድ ዜናዌ፣
ቅብዕኒ ሐፈ ሥዕልኪ ወፈውስኒ እምደዌ፣
እስመ በኀምዙ አቍሰለኒ አርዌ::

*ማርያም ሆይ የተክል ዛፍ ለምልማና አብባ ደስ እንደምታሰኝ ሥዕልሽ ሥጋን የለበሰች መስላ ታየች የተአምርሽን ዜናም ለልጅ ልጅ የምነግር እሆን ዘንድ የሥዕልሽን ወዝ ቀብተሽ ከበሽታ አድኚኝ አውሬ (እባብ) የተባለ ዲያብሎስ በመርዙ ኃጢአት አቍስሎኛልና* ዘፍ.3.1-10::

25) ጌታ፣ ከክፉ ነገሮች ሁሉ፣ አጥብቆ የሚጠላው በወንድማማች መካከል እየገባ ጠብን የሚዘራ ሰውን ነው ምሳ.1.6-16::



ጀ፴:-130 ቦ፡ አመ ትትረከብ ምስለ ቃለ ነገር ጥዑም፣
ወቦ፡ አመ ትትረአይ በለቢሰ አባል ልምሉም፣
ሥዕልኪ ማርያም ጽጌ ተአምራ (ጽጌ ተአምር) አዳም፣
ወአመ ዘበጣ በሰይፍ አይሁዳዊ ርጉም፣
እምኔሃ አንፀፍፀፈ ደም::

*ማርያም ሆይ ሥዕልሽ ደስ ከሚያሰኝ ንግግር ጋር የምትገኝበት ጊዜ አለ (ነበረ) የለመለመ አካልንም የለበሰች መስላ የምትታይበት ጊዜ አለ (ነበረ) ተአምሯም ፍጹም ደስ የሚያሰኝ ነው ክፉ አይሁዳዊ ሰውም ሥዕልሽን በሰይፍ በመታት ጊዜ ከእርሷ ደም ጠብ፣ጠብ፣ አለ (ፈሰሰ)::*

## ከተቈረጠችው ሥዕል የተሰማው ድምጽ

(ታሪኩ):- ቀደም ሲል (በገጽ 30 ላይ) እንደተገለጸው ጼዴንያ በምትባል አገር ያለች ማርታ የምትባል ደግ ሴት ነበረች ንጉሥ ሰሎሞን ለታቦተ ጽዮን ማደሪያ የሚሆን ቤተ መቅደስን እንደሠራ ሁሉ 2ኛ.ነገ.5.1-17. እርሷም ለእመቤታችን ሥዕል ቤትን አሠርታ አክብራ አኖረቻት:: ሌሊትና ቀንም በቀኝና በግራ ዕለት ዕለት (ዘወትር) መብራትን ታበራላትና እየሰገደች እጅ ትነሳት ነበር፣ ሥዕሏም ሥጋን የለበሰች ትመስልና፣ ከእርሷም ወዝ ይወጣ፣ ከወዝዋ የተቀቡም ሁሉ ከደዌያቸው ይፈወሱ ነበር:: አፍርንጊ በምትባል አገርም እጅግ የከበረ አንድ ነጋዴ ነበርና! ሥጋ የለበሰች የምትመስለውን ይህቺን የእመቤታችንን ሥዕል ዜና በሰማ ጊዘ ፈጽሞ ደስ አለውና ገንዘቡን ሁሉ ትቶና ደሃ መስሎ ጼዴን ወደምትባለው አገር ሄዶ የእመቤታችንን ቤተክርስቲያን (ለ2) ዓመት ያህል ሲያገለግል ከኖረ በኋላ ሥዕሏን ከመውደዱ የተነሣ መስረ ባይመቸው ሰይፍ ይዞ እጁን በመስኮት አዘልቆ ከሥዕሏ የሥ ቍራጭን ያህል ቈረጠ:: ያን ጊዜም ከሥዕሏ ደም ወጣ (ጠብ ጠ አለ) ሰዎችም ይገድሉት ዘንድ ሲይዙት እኔን ከመውደዱ የተነ ክብር ሊሆነው ወስዷል እንጂ፣ በክፋት አላደረገውምና ተዉ አትግደሉት የሚል ድምጽ ከሥዕሏ ተሰማ:: ከሥዕሏ የተቈረጠውን

(26) እስራኤል፣ በልብሳቸው ጫፍ ላይ ሰማያዊ ቀለምን ለምን አደረጉ? →

www.ethiopianorthodox.org

የሥዕሏን ክፍልም ከተቈረጠበት ቦታ ቢገጥሙት ተጣብቆ እንደ ቀድሞው ሆነ (177 ተአምረ ማርያም):: የእመቤታችን ሥዕል የምታደርገው ተአምር አሁንም እጅግ ብዙ ነውና፣ ከዕለታት አንድ ቀን ደግሞ አንድ አረማዊ ሰው የሰውን ገንዘብ እወስዳለሁ ብሎ ከሰዎች ጋር ሲጨቃጨቅ ሰዎቹ ቢረቱትና ቢበሳጭ ከአንዲት ቤተ ክርስቲያን ሄዶ የእመቤታችንን ሥዕል በተሳለ ሰይፍ መትቶ ከጥልቅ ጉድጓድ ጨምሯት ሲመለስ፣ ልብሱን ደም ነክቶት አንድ ክርስቲያን አይቶ "አንተ የተረገምክ! ሰው" በእውነት የጻድቅ ሰው ደም አፍስሰሃል፣ በላይህ ላይ የተረጨውን እና እየመሰከረብህ ያለውን ደም እስኪ ተመልከት! ሲለው እሱም ደንግጦ እኔ እኮ የጻድቅ ሰው ደም አላፈሰስኩም፣ አልገድልኩምም:: ነገር ግን የድንግል ማርያምንና የልጇን ሥዕል በሰይፍ መትቼ ቀድጃለሁ አለው:: ክርስቲያኑ ሰውዬም በዚያች አገር ወደአለ ዳኛ ወሰደውና ሥዕሏን የት ጣልካት ሲሉት፣ እንዴት አድርጎ እንደመታት እና ከጥልቅ ጉድጓድ እንደጣላት ነገራቸው:: ሰዎችም ሥዕሏን ወደጣለበት ጉድጓድ እየሮጡ ቢሄዱ፣ ሥዕሏ ከተቈረጠው ቦታ ላይ እንደ ክረምት ውሃ ደም ሲፈስስ አይተው ከጉድጓዱ አውጥተው ቀድሞ ወደ ነበረችበት ቦታ በእልልታ መልሰው አስቀመጧት፣ በየዓመቱ መስከረም (8) ቀንም ያከብሯት ጀመር፣ ይህ ሰውም ንስሓ ገብቶና ተጠምቆ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ በቅንነት ሲያገለግል ኖሮ በክብር ዐረፈ (294 ተአምረ ማርያም)::

ፀ፴፩፦131 ኀበ ወረቀ ብእሲ ጽጌ ከርሥኪ መሥዋዕተ፣
በሐቂፈ ሕፃን ሥዕልኪ ተረክበት ክሡተ (ክሥተ)፣
ወካዕበ ኮነት ምስለ ወይነ ምሥጢር ኅብስተ፣
እለ ርእዩ ወእለ ሰምዑ መንክረኪ ዘንተ፣
ለተአምርኪ ማርያም ወሀቡ ስብሐተ::

(27) ጌታ፣እስራኤል በልብሳቸው ጫፍ ላይ ሰማያዊ ቀለምን እንዲያደርጉ ያዘዘበት ምክንያት፣ሰማይ የመሰለ ባህርን አሻግሬ፣ ሰማያዊ ሕግን ሠራሁላችሁ ሲል ነው ዘፀ.15.38 ንባብና ትርጓሜው::



ማርያም ሆይ አንድ ሰው የማሕፀንሽ ፍሬ የሆነ የጌታ ሥጋው
ደሙን ተቀብሎ በተፋበት ቦታ ሥዕልሽ ሕጻንን ታቅፋ ከሥጋ
ከደሙ ጋር በግልጽ ታየች (ግልጽ ሆና ተገኘች) ይህን ድ
ሥራሽንም ያዩና የሰሙ ሁሉ ለተአምርሽ ምስጋናን አቀረቡ::

## የእመቤታችን ሥዕል፣ በንብ ቀፎ ውስጥ ስለመታየቷ

(ታሪክ) ብዙ ንብ የነበረው አንድ ሰው ወደ አንዲት ሥራየኛ (
ጠንቋይዋ) ሴት ሄዶ፣ ንቤ ከሰው ሁሉ የበለጠ ይበዛልኝ ዘ
የምሠራውን ሥራ እንድትመክሪኝ እለምንሻለሁ አላት፣ ያቺ ሴት
እኔስ ሥጋውን እና ደሙን በተቀበልህ ጊዜ ካፍህ አውጥተህ በ
ቀፎ ውስጥ ጨምረው፣ ብዙ ንብ፣ ሰምና ማርም ይሆንልሃል
እመክርሃለሁ አለችው:: እሱም በነገረችው (በ2ተኛው) ቀን
ቤተክርስቲያን ሄዶ ሥጋውንና ደሙን ከተቀበለ በኋላ እንደ ነገረች
ሥጋውንና ደሙን ከአፉ አውጥቶ በንቡ ቀፎ ውስጥ ጨምሮ
ወደቤቱ ገባ:: (በ2ተኛው) ቀንም ይህ ሰው በንቡ ቀፎ ው
ከጠንቋይዋ እንደተነገረው አልሆነለትም:: ነገር ግን በዚያ ፈ
ፍጹም (ታላቅ) ብርሃንን እና የእመቤታችንን ሥዕል አየ፣ ሥዕሏ
ከፀሐይና ከጨረቃ ይልቅ የሚያበራ ልጅን ታቅፋ ነበር:: ይ
ድንቅ ተአምርም በዓለም ሁሉ ተነገረች፣ ታወቀችም (174 ተአ
ማርያም)::

ፀ፴፪፦132 ተአምረ ወልድኪ ጽጌ ለዓይንየ ይኤድማ፣
ወእምኔሁ ፈድፋደ ላህየ ሥዕልኪ ሥርጉተ ግርማ፣
ለገነተ ትንቢት ማርያም ዘመነ ጽጌሃ ወቀስማ፣
ይኅልዩ ለኪ እስራኤል በጥዑም ዜማ፣
ታሕተ በለሶሙ ወወይኖሙ አዕረፉ እምጻማ::

ለተክል ቦታ ትንቢት የአበባዎና የፍሬዎ ዘመን የሆንሽ (
ከሥጋሽ ሥጋን፣ ከነፍስሽ ነፍስን ነሥቶ አዳምን ከነልጆቹ
ገነት እንዲመልሰው ዘፍ.3.22. ትንቢት የተነገረልሽ እና ትንቢቱ
ተፈጽሞ አዳም ከሲኦል ወደ ገነት የተመለሰብሽ) ሉቃ.23.39-40. ማርያም ሆ

(28) እስራኤል፣ ከግብፅ ከወጡ ጀምሮ ስንት ጊዜ ሰፈሩ? →

www.ethiopianorthodox.org

*የልጅሽ የተአምር አበባ ዓይኑ ልቡናዬን ደስ ያሰኛታል ከእርሱም ይልቅ በእጅጉ የመወደድ ግርማን የተሸለመች የሥዕልሽ መልክ ዓይኔን ደስ ያሰኛታል፣ እስራኤልም ደስ በሚያሰኝ ዜማ ይዘምሩልሽ ዘንድ ከበለሳቸውና ከወይናቸው በታች ዐረፉ (ተጠለሉ)፡፡*

(ታሪኩ) በነገሥታቱ በሰሎሞን፤ በሕዝቅያስና በዘሩባቤል ዘመነ መንግሥት እስራኤል ዘሥጋ የተባሉ ሁሉ ከመከራ ሥጋ የዳኑበትና አንዱ በአንዱ ላይ ጦር ሳያነሳ ዘመኑ የሰላም ዘመን ሆኖ እስራኤል እየአንዳንዳቸው ከበለሳቸውና ከወይናቸው ሥር (40) ዘመን በሰላም ያረፉበት ታሪክ ሲሆን፣ 1ኛ.ነገ.4፥25፣ ሚክ. 4.4. እስራኤል፣ ደስ በሚያሰኝ ዜማ ይዘምሩልኝ ማለቱም፣ አዳም ፈጣሪውን በድሎና ፈርቶ ሲሸሽግ፣ ጌታም አዳም! ወዴት ነህ ብሎ ቀኑ ሲመሽ በገነት ውስጥ ድምፁን ማሰማቱ፣ (ከአዳም ጋር መነጋገሩ)፣ ዘፍ.3.8-10. የዚህ ኃይለ ቃል ምሥጢር፣ በመጽሐፈ ቀሌምንጦስ ምዕራፍ 3. ቊጥር 19-21፣ በመጽሐፈ ሲራክም ምዕራፍ 24. ቊጥር 6-9. እንደተጻፈ፣ በሐሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወለድ እምወለተ ወለትከ፣ "በአምስት ቀን ተኩል ማለትም በ5,500 ዘመን የልጅ ልጅህ ከምትሆን ከድንግል ማርያም ተወልጄ፣ (ሥጋን ለብሼ)፣ በመስቀል ተሰቅዬ አድንሃለሁ ብሎ" የ5,500 ዘመን የተስፋ ቃል መስጠቱ ነበርና፣ የዚህ ዘመን ፍጻሜ ሲደርስ ጌታ ከሴት (ከድንግል ማርያም) ተወልዶ ገላ.4.4. በመስቀል ላይም ተሰቅሎ እርሱን (አዳምን) ወክሎ አባት ሆይ በመጽሐፍ የተነገረው ሁሉ ተፈጸመ ብሎ በለበሰው ሥጋ ወደ ባሕርይ አባቱ ወደ አብ ሲጸልይ ዮሐ.19.28. የሥርዓተ ቅዳሴ ትርጉም እንደተናገረውም፣ አዳም ከጌታ የተሰጠው የተስፋ ቃል እንደተፈጸመ በዚህ ተረድቶ፣ ዛሬ የአዳም ምሳሌ ሆኖ በቅዳሴ ጊዜ ዲያቆኑ፣ ተንሥኡ ለጸሎት (ለጸሎት ተነሡ)፣ የሚለውን ጸሎት አባታችን አዳም በሲኦል

(29) እስራኤል፣ ከግብፅ ወጥተው ከነዓን እስኪገቡ ድረስ (42) ጊዜ ሰፈሩ፣ይህም ከአብርሃም እስከ ክርስቶስ ልደት ድረስ ለአለው (ለ42) ትውልድ ቊጥር ምሳሌ ነው ማቴ.1.17-18 ንባቡና ትርጓሜው፡፡

www.ethiopianorthodox.org



የነበሩ ነፍሳትን በጸሎት ለማትጋት፣ ተንሥኡ ለጸሎት (ለጸሎ[ት] ተነሡ) ብሎ ሲያውጅ፣ የዛሬ ምእመናን ምሳሌ የሆኑ በገነት የነበ[ሩ] ነፍሳትም፣ እግዚኦ ተሣሃለነ (አቤቱ ይቅርበለን) ሲሉ የዛሬ ቄ[ስ] ምሳሌ የሆነው ጌታም፣ ወዲያው በአካለ ነፍስ ሲኦል ወርዶ፣ ሰላ[ም] ለኵልክሙ (ሰላም ለሁላችሁ ይሁን) ብሎ የመለኮቱን ብርሃ[ን] በሲኦል ሲነዛ (ሲገልጽ)፣ ነፍሳትም መልሰው ምስለ መንፈስከ (ከመንፈስህ ጋር፣ እንደቸርነትህ ይደረግልን) ብለው ከእስራኤ[ል] ወገን ከተገኘች ከድንግል ማርያም በተወለደ በጌታ ቸርነት ከሲኦ[ል] መከራ ወጥተው ገነት ገብተውና ደስ ተሰኝተው በሰላም ይኖራሉ[ና] ነው፡፡

> ፻፴፫፡-133 ዕቍረ ማየ ልብን ሊተ ዘወልድ እኍየ፣
> ኅበ ተኀሊ ወትቤ ተአምረኪ ሠናየ፣
> ገቢራ ትርሢተ ልብሰ በዓል ጽጉየ፣
> እንዘ ትነጽፍ ዘርቤታተ ወትነሰንስ መጽርየ፣
> ለክብረ ሥዕልኪ ድንግል ትሰግድ ነፍስየ፡፡

*ድንግል ሆይ ነፍሴ የልጅ ወንድሜ የተቋጠረ የነጭ ዕጣን ሽቱ ለእ[ኔ] ነው ብላ መልካም ተአምርሽን በአሰበችበት ቦታ የበዓል ልብስ ለብሳና የከበረ ምንጣፍን አንጥፋ፣ የቀጋ አበባንም ነሰንሳ (ይህ ቃ[ል] ቀድሞ በንጉሥ ሰሎሞን እንደተነገረ መኃ 1.14፤4-14 የእግዚአብሔርን ልጅነት አግኝታ፣ እርሱንም መስላ) ለሥዕል[ሽ] ክብር ትሰግዳለች ፡፡*

> ፻፴፬፡-134 ከመ ይትፌሣሕ ሕጻን ሶበ ይሬኢ እሞ፣
> እትፌሣሕ ሥዕለኪ (እትፌሣሕ አንስ ሥዕለኪ) በርእይ ወተሳልሞ፣
> ተአምረ ላሕኪ ድንግል ለፀሐየ ቀትር እስከ አጽለሞ፣
> እስመ ፍቅርኪ ጽጌ ትፍሥሕት ለአስካልኪ አሕመሞ፣
> ለቤዛ ዚአየ ከመ ይክዐው ደሞ፡፡

*ድንግል ሆይ ሕጻን ልጅ እናቱን ባየ ጊዜ እንደሚደሰት፤ እኔ[ም] ሥዕልሽን በማየትና በመሳለም እደሰታለሁ የኀዘንሽ ተአምር፣*

(30) መስቀል፣ (የመስቀል ምልክት)፣ ለመጀመሪያ ጊዜ በማን እጅ ታየ? →

*የቀትር ፀሐይን እስከ አጨለመው ድረስ ደስ የሚያሰኝ ፍቅርሽ! (ሰውን ወደ ወደዚህ ዓለም የመጣና) እኔን ለመዋጀት ደሙን ያፈሰሰ ዘንድ፣ ልጅሽን የመስቀል መከራ እንዲቀበል አድርጎታልና ኢሳ. 52.3፣ 1ኛ.ዮሐ.1.7::*

ፀ፴፭፡-135 ሶበ ሰዐመ ጎፍረተ ትክት ቅድመ መዋዕለ ንጽሕ ሱባዔ፣
(ሶበ ተርጐመ ቃለ ወንጌል ቅድመ ንጉሥ እንበለ ይግበር ምማዔ)፣
ተአምረ ፍቅርከ ያርኢ ወያስተሐፍር ጸላዔ፣
ማርያም ሥዕልኪ ለዮሐንስ ጽጌ ትንሣኤ፣
ወደሰቶ ወአእኰተቶ ቅድመ ገጸ ኲሉ ጉባኤ፣
አፈ ወርቅ እንዘ ትብል ጊዜያተ ክልኤ::

*ማርያም ሆይ ዮሐንስ የፍቅርሽን ተአምር ይገልጽና ጠላትን ያሳፍር ዘንድ (ከ7) ቀን መንጻት በፊት ዘሌዋ.12.2-4. ደም የሆነ የሴት አካልን በሳመ ጊዜ (የፍቅርሽን ተአምር ይገልጽና ጠላትን ያሳፍር ዘንድ አርቃድዮስ በሚባል ንጉሥ ፊት ሳያፍር የወንጌልን ቃል በተረጐመ ጊዜ) ሥዕልሽ የትንሣኤ አበባ የሆነ፣ (ትምህርቱ ደስ የሚያሰኝ) ዮሐንስን «2» ጊዜ አፈወርቅ፣ አፈወርቅ እያለች በሕዝቡ ፊት ፈጽማ አመሰገነችው::* "ሶበ ተርጐመ ቃለ ወንጌል ቅድመ ንጉሥ እንበለ ይግበር ምማዔ፣ ማለትም ዮሐንስ፣ በንጉሥ አርቃድዮስ ፊት ሳያፍር (ሳይፈራ) የወንጌልን ቃል በተረጐመ ጊዜ" የሚለውን ቃል ታሪኩን ወደፊት ከምናገኘው ከዮሐንስ አፈወርቅ ታሪክ አምጥተው ሊቃውንት አባቶች ከዚህ አስገብተውታል::

## ዮሐንስ! ዳንኤልና አፈወርቅ እንዴት ተባለ?

(ታሪክ) ዮሐንስ አፈወርቅ ሲፋኒዶስ (ሴኮንዶ) ከሚባል አባቱ አትናስያ (አንጡሳ) ከምትባል እናቱ (በ347) ዓ.ም መስከረም (9) ቀን በአንጾኪያ ተወለደ አባቱ ወታደር ነበር በሕጻንነቱ ዐረፈ እናቱ ብቻ አሳደገችው ሥጋዊ ጥበብን (ፍልስፍናን) ከተማረ በኋላ ብሉይንና ሐዲስን ተማረ መነኮሰም እናቱም ዐረፈች በዚህ ጊዜም የአባቱንና የእናቱን ሀብት ምንም ሳያስቀር ለነዳያን መጽውቶ ተመልሶ ወደ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ገባ ገና በዲቁና መዓርግ

(31) መስቀል (የመስቀል ምልክት)፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የታየ ዓለም በተፈጠረባት መጋቢት (29) ቀን እሑድ በመላእክት እጅ ነው (የእሑድ መጽሐፈ አክሲማሮስ ክፍል አንድ)::



እያለም የኦሪትንና የነቢያትን መጻሕፍት ተረጐመ:: ከዕለታት አን ቀን ተግቶ ሲጸልይ የጌታ መልአክ ሐዲስ ዳንኤል ብሎ አጽናና ሐዲስ ዳንኤል የተባለበት ምክንያትም ነቢዩ ዳንኤል የጠ የናቡከደነፆር ሕልሙንና ትርጕሙን በመንፈስ ቅዱስ ተገልጾለ እንደተረጐመ ሁሉ (ዳን 2.1-49) ዮሐንስ አፈወርቅም፣ አፈወር ከመባሉ በፊት ዘመነ ሰማዕታት በተባለው በዲዮቅልጥያኖስ በመክስምያኖስ ዘመነ መንግሥት ንባቡና ትርጕሙ ጠፍ የነበረውና ራእየ ዮሐንስ የተባለው መጽሐፍ፣ እንደነበረ ማለት ቀድሞ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ የደረሰውና የጻፈው ቃል በመንፈ ቅዱስ ተገልጾለት አንድ ቃልን ሳይጨምር እና ሳይቀን ተናግሮታል:: ስለዚህ

ዮሐንስ አፈወርቅ ሐዲስ ዳንኤል ተባለ ፊላትያኖስ (ፍላቢያኑስ ከተባለው ከአንጾኪያ ሊቀጳጳሳትም የቅስና ሥልጣንን ተቀበለ፣ በዚ መዓርግ እያለም መጻሕፍተ ሐዲሳትን ተረጐመ፣ (በ43) ዓመቱ የጵጵስና ሹመትን ቍስጥንጥንያ በምትባል አገር ተሾሞ ብዘ ድርሳናትና ተግሣጻትን ደረሰ (ጻፈ):: አፈወርቅ የተባለበትን ምክንያት ከዚህ ይናገሩታል::

1ኛ. ይህ ሰው፣ ዮሐንስ ተብሎ በሚጠራበት ጊዜ ሲያስተም ትምህርቱ ደስ ቢላቸው ምእመናን ይህስ አፈወርቅ ነወ ብለውታል::

2ኛ. በቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል ምዕ.1.25. የበኵር ልጅዋ እስክትወልድ ድረስ ዮሴፍ፣ እጮኛው ማርያምን አላወቃት የሚለውን ቃል፣ አርቃድዮስ የሚባል ንጉሥ ትርጕሙ ጠይቆት ሊቁ ዮሐንስ ሲተረጕም እንዲህ አለ፣ እመቤታች ጌታን ከመውለዷ አስቀድሞ ዮሴፍ ወላዲተ አምላክ እንደሆነች አላወቀም ምክንያቱም ከዚያ በፊት ያለማንኙነት፣በድንግል የፀነሰች ሴት የለችም ነበርና (አያውቅም ነበርና)::

የድንግል ማርያም ፅንስም በድንግልና መሆኑ ለዓለም

(32) መስቀል፣ ድል ማድረግ የጀመረ መቼ ነው? ⟶

www.ethiopianorthodox.org

እንግዳ (አዲስ ምሥጢር) ነውና፣ አምላክን እስከምትወልድ ድረስ የአምላክ እናት መሆኗን በእርግጥ አላወቀም፡፡ ነገር ግን ኮከብ ከያዕቆብ ይወጣል (ኮከብ ክርስቶስ ከያዕቆብ ዘር ይወለዳል) ተብሎ የተነገረ ትንቢት ዘኍ.24.17. ተፈጽሞ ጌታ ሲወለድ፣ የሰማይ ሰራዊትም ለምስጋና ሲወጡና ሲወርዱ (በምስጋና ሲሰግዱ)፣ ባየ ጊዜና ኖሎት (እረኞች) ከመላእክት ጋር ሲያመሰግኑ በሰማ ጊዜ፣ ሰብአሰገልም ሰግደው ወርቅ፣ ዕጣን፣ ከርቤ ሲያቀርቡለት አይቶ፣ ከድንግል የተወለደውም የነገሥታት ንጉሥ እንደሆነ ሲረዳ የአምላክ እናት መሆኗን አወቀ ማለት ነው ብሎ ምሥጢሩን አስፋፍቶ በትክክል ተርጒሞ ሲጨርስ፣ በመስኮት ያለችና በወርቅ የተሣለች የእመቤታችን ሥዕል ከመስኮት ወርዳ (3) ጊዜ ራሱን ዞራ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ አፈ ዕንቊ፣ ዕንቈ ጳዝዮን (ትምህርትህና አነጋገርህ እንደ ወርቅ እና እንደ ዕንቊ የተወደደልህ ዮሐንስ) ሆይ መልካምን ተናገርክ አለችው፡፡ ንጉሥ አርቃድዮስም ይህን ሰምቶ እጅግ ተደነቀና ከእንግዲህ በኋላ ስሙ «አፈወርቅ» ይባል ብሎ አዋጀ፡፡ ስለዚህ አፈወርቅ ተባለ ማቴ.1.18-25 (የዮሐንስ አፈወርቅ ድርሳን ንባቡና ትርጓሜው፣ እንዲሁም 157 ተአምርና የግንቦት 12 ቀን መጽሐፈ ስንክሳር)፡፡

ጀ፴፮፡-136 ርኅራኄኪ ማርያም ቀሢፈ ሕጻን አኅደጎ፣
ለመልአክ ብኪ ዘተማሕጸነ ትእዛዘ ጽጌኪ በአንትትጎ፣
እምድኅረ ተሥዕኖ ዐሪግ ለቀዊም ኀበ ይዛወጎ፣
ሳሙኤል ሶበ ጸለየ ደብረ ቀልሞን ዐሪጎ፣
ኃይለ ተአምር ዘሥዕልኪ ሰማየ መዘጎ፡፡

*ማርያም ሆይ፣ ርኅራኄሽ ይገለጽ ዘንድ ሕጻንን ከመቅሠፍ (ከመግደል) የተማፀነብሽ መልአክን አስተወው የልጅሽን ትእዛዝ በማጉደሉ ምክንያት እንደ ወገኖቹ (እንደ መላእክት) መቆምና ማረግ ከተሣነው በኋላ ሳሙኤል ቀልሞን ወደተባለ ተራራ ወጥቶ በጸለየ ጊዜ፣ የሥዕልሽ ድንቅ ተአምር ወደ ሰማይ ዐሳረገው፡፡*

(33) መስቀል፣ ድል ማድረግ የጀመረው ዓለም በተፈጠረ (በ4ኛው) ቀን ሚያዝያ (2) ቀን ረቡዕ ነው፣ ይህም መላእክት ከዲያብሉስ ጋር በሰማይ ጦርነት (ሰልፍ) ባደረጉ ጊዜ ነው ራእ.12.7፣ (የእሑድና የረቡዕ መጽሐፈ አክሲማሮስ)፡፡



## ምድራዊው:- ሰማያዊውን ስለ መርዳቱ

(ታሪክ) ጻድቁ አባ ሳሙኤል በግብጽ ደቡብ ደክሉባ በሚባል መንደር ተወለደ አባቱ ካህን ነበር (በ14) ዓመቱ በአስቄጥስ ገዳም መነኰሰ ከታናሽነቱ ጀምሮም እንደ ነቢዩ ሳሙኤል 1ኛ.ሳሙ.2.18. ቤተ እግዚአብሔርን እያገለገለ ያደገ ሲሆን፣ ሰማያዊ መልአክን አማልዷል ይህም ጌታ ገምኑዲ በምትባል አገር በቅዳሴ ጊዜ ወዲያና ወዲህ እየተመላለሱ አውከው የነበሩ ሕጻናትን ቅሠፉ ብሎ መላእክትን ላከ ቀውስጦስ የሚባለው መልአክም መልከ መልካም ሕጻንን ከነጌጡ አገኘ ይህንንስ የፈጠረው ይግደለው ብሎ ትቶታል፡፡ የቀሩት መላእክት ግን የታዘዙትን ፈጽመው ወደ ሰማይ ሲያርጉ እሱ ክንፉ ተሰብሮና ኃይል አጥቶ ወደ ሰማይ ሳያርግ ቀረ ወደ ማዶ አሻግሮ ቢያይ ቀልሞን በሚባል ተራራ የብርሃን ምሰሶም ተተክሎ አየ ይህቺ ቦታ ከፈጣሪዬ ጋር አስታራቂ ትሆነኛለች ብሎ ተጎትቶ ሄዶ ከደጀ ብርሃን (ከቤተልሔም) ወደቀ ዲያቆን ለተልዕኮ ከፍቶ ቢገባ ከዚያ ወድቆ አገኘው አንተ ምድራዊ ነህን ሰማያዊ? አለው ቀውስጦስም ግብሬ ምድራዊ አደረገኝ እንጂ፣ ተፈጥሮዬስ ሰማያዊ ነበር አለው አሁንም ሄደህ ለአባ ሳሙኤል ንገርልኝ አለው ሄዶ ነገረው እሱም ደወል መትቶ ሕዝቡን ሰብስቦ (41) ኪርያላይሶን (አቤቱ ይቅር በለን)፣ (41) በእንተ ማርያም (ስለ ድንግል ማርያም ብለህ ይቅር በለን) የሚል ጸሎትን አድርሶ ሄዶ ከሥዕለ ማርያም ተማጸነ፣ እመቤታችንም አባ ሳሙኤልን በቀኝ እጅህ ቀኝ ክንፉን፤ በግራ እጅህ ግራ ክንፉን ይዘህ፣ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ስም ተነሥ በለው አለችውና እንደነገረችው ሄዶ በቀኝ እጁ ቀኝ ክንፉን፤ በግራ እጁ ግራ ክንፉን ይዞ በፈጣሪህ በእግዚአብሔር ስም ተነሥ ቢለው፣ ቀውስጦስ (ይህ መልአክ) የቀደመ ኃይሉ ተመልሶለት ማኅበሩን በረድኤት እንዳልለያችሁ ስሜን ከአባ ሳሙኤል አትለዩት ብሏቸው ወደ ሰማይ ዐረገ (277 ተአምረ ማርያም)፡፡ ይህ (አባ ሳሙኤልም)

(34) የጌታ መስቀል፣ ከተቀበረበት በንግሥት ዕሌኒ ከመውጣቱ በፊት ለማን ታየ? →

www.ethiopianorthodox.org

(በ451) ዓ.ም በኬልቄዶን የተደረገውን የክህደት ቃለጉባኤ ቢልኩለት አይቶ በእሳት ያቃጠለ ጻድቅ ነው።

፻፴፯፡-137 ሥዕልኪ ጽግይተ ላህይ ዘከመዝ ትኤድም በዓለም፣
እፎ ይሤኒ በሰማይ ላህየ ገጽኪ ማርያም፣
ሐሤተ ትእምርትኪ እጽገብ አስተርእዩኒ በሕልም፣
እስመ አውዐየኒ ነደ ፍቅርኪ አፍሐም (ፍህም)፣
አጥፍኦቶ ዘኢይክል ዝናም።

*ማርያም ሆይ መልኳ አበባ የመሰለ (ደስ የምታሰኝ) ሥዕልሽ በዚህ ዓለም እንዲህ የምታምር ከሆነ! በሰማይማ! የፊትሽ መልክ ምን? (እንዴት?) ያምር! (ክብርሽ እንዴት ይበልጥ)? የአንቺን ደስታ እጠግብ ዘንድ በሕልም ተገለጪልኝ፣ ዝናም ሊያጠፋው የማይቻለው እሳት ፍቅርሽ አንድዶኛልና።*

፻፴፰-138 አመ ትበርቂ በደብረ ምጥማቅ ሐምሰ ዕለታተ፣
ትእምርተ ገጽኪ ይርአይ እስከ ይትነሣእ ዘሞተ፣
ሚ፡መጠነ ማርያም ታስተፌሥሒ ትፍሥሕተ፣
ኅድጊሰ ጽጌ ፍቅርኪ በጊዜ ንቃሁ መዓልተ፣
ብፁዕ ዘርእየኪ በሕልሙ ሌሊተ።

*ማርያም ሆይ የፊትሽን መልክ (ሰማያዊ ክብርሽን) ያይ ዘንድ የሞተ ሰው እስኪነሣ ድረስ ደብረ ምጥማቅ በምትባል ቦታ (ለ5) ቀን ያህል በተገለጽሽ ጊዜ ምን ያህል ደስ ታሰኚአለሽ። በቀን የታየውና ደስ የሚያሰኝ ፍቅርሽን የገለጽሽበት ተአምር ይቅርና፣ (ይህንን ተዪና፣) ሌሊት በሕልሙ ያየሽ ምስጉን ነው።*

## የሞቱና ያልሞቱ ሰዎች በዓይን ስለመተያየታቸው

(ታሪክ) ፊልጵስዩስ በምትባል አገር ታላቅ ቤተ ክርስቲያን በአንቺና በእኔ ስም ተሠርቶ ለመነኮሳት ገዳም ይሆናል ብሎ ጌታ ለእናቱ

(35) በአይሁድ የተቀበረው የጌታ መስቀል፣ በንግሥት ዕሌኒ ከመውጣቱ (ከ15) ዓመት በፊት ሰይጣን ከእባብ ምስል ጋር ለአሕዛብ ንጉሥ ለድዮቅልጥያኖስ እንደታየው ሁሉ፣ ለክርስቲያኑ ንጉሥ ለቈስጠንጢኖስ በአራት ከዋክብት አምሳል (በ312) ዓ.ም በሰማይ ሲያበራ ታየ (የመጋቢት 28 ቀን መጽሐፈ ስንክሳር፣ የቤተክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ እና መጽሐፈ ምሥጢር ምዕ.27፡ ቍ.16-17)።



አስቀድሞ በስደቱ ጊዜ እንደተናገረና ትንቢቱ ተፈጽሞ ቤ
ክርስቲያኗ ተሠርታ ደብረ ምጥማቅ ተብላለች፣ በየዓመቱ ከግንቦ
(21) ቀን እስከ (25) ቀን ድረስም (ለ5) ቀን ያህል ከግብጸ
ከኢትዮጵያ፤ ከአርማንያና ከሶርያ፣ ከሌሎች አገሮችም ሁ
መጥተዉ ተሰብስበዉ ሳሉ፣ ገዳሙ የተቃጠለ እስኪመስል ድ
ድንገት ከሰማይ ልዩ ብርሃን ወረደ፣ የተሰበሰቡ ሰዎችም እጀ
አደነቁ ከሰማዕታት ወገንም በንጉሥ ዳክዮስ ዘመነ መንግሥ
ማለትም በ250 ዓ.ም በተወለደ (በ25) ዓመቱ በሰማዕትነት ያረፈ
ቅዱስ መርቆሬዎስ፣ (በ277 ዓ.ም) ያረፈው ቅዱስ ቴዎድሮስ እ
(በ304) ዓ.ም ያረፈው ቅዱስ ጊዮርጊስ ይታዩ ነበር፣ ማንም ስ
ቀድሞ በሕይወቱ እያለ የሚያውቀውንና የሚሻውን ሰው ከሞ
ተነሥቶ ያይ ነበር (በ5) ቀን ውስጥም እመቤታችን ለክርስቲያኖች
ለእስላሞች እየተገለጸች ትታይ ነበር የግንቦት (21) ቀን መጽሐፈ ስንክሳር
93ኛ ተአምረ ማርያም፣እንዲሁም (የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በሉሌ መልአኩ 1986 ዓ.ም

፻፴፱፡-139 ቀሡታተ ይጽዐን በአንበሳ እብነኒ በርእሰ ሰይጣን ተቃራኒ
አብሖ ለአሮን ሶርያዊ ኃይለ ፍቅርኪ ሰፉኒ፣
ጽጌ ደብረ ምጥማቅ ማርያም ተአምርኪ ኖኅኒ፣
ዘይገኒ ለዕበይኪ ኵሉ ያገኒ፣
ወአጋንንተ ከመ ገብር ይቀኒ።

*የደብረ ምጥማቅ አበባ የሆንሽ (ደብረምጥማቅ በምትባል ቦ
ተአምርሽን የገለጽሽ) ማርያም ሆይ ገዥ የሆነ የፍቅርሽ ኃይ
ማድጋዎችን (እንስራዎችን) በአንበሳ፤ ድንጋይንም የበጎ ሥ
ተቃራኒ በሆነ በሰይጣን ራስ ላይ ይጭን ዘንድ ሶርያዊው አሮንን
አሰለጠነው ተአምርሽም በዝቶ ተትረፈረፈልኝ፣ ለክብርሽ ታላቅነ
የሚገዛም ሁሉን ያስገዛለታል፣ አጋንንትንም እንደ አገልጋይ ይገዛል*

(36) ቅዱስ ያሬድ፣ መስቀል አብርሀ በከዋክብት አሰርገወ ሰማየ እምኵሉሰ ፀሐየ አርአየ
"መስቀል፣ እንደ ከዋክብት አበራ፣ ሰማይንም በብርሃን አስጌጠ፣ ብርሃኑም ከፀሐ
ብርሃን ይልቅ በለጠ" አለ፣ (ጾመ-ድጓ እና የሥርዓተ-ቅዳሴ መግቢያ)።

www.ethiopianorthodox.org

## አንበሳ ውሃን ስለመቅዳቱ

(ታሪክ) ሶርያ በምትባል አገር ከልጅነቱ ጀምሮ የመፈወስና ድንቅ ተአምራትን የማድረግ መንፈሳዊ ሀብት የተሰጠው አሮን የሚባል ጻድቅ ሰው ነበር ይኸውም እንግዶች መነኮሳት ወደ እርሱ በመጡ ጊዜ የርግብ ግልገሎችን አብስሎ ያቀርባል፣ ሥጋ አንበሳም ባሉት ጊዜ ግን በርግቦቹ ላይ በመስቀል ምልክት አማትቦ ርግቦችን እንዲበሩ ያደርግ ነበር፣ በተራራ ላይም ገዳምን ሠራ ውሃውም ከተራራው በታች የራቀ ነበርና፣ ባማተበና በጸለየ ጊዜ ውሃውን ስቦ ከተራራው ላይ ያወጣዋል በአንዲት ቀንም ሰይጣን በተንኮሉ ሊአጠፋው ወደ እርሱ መጣ የአሮንም (2) በር ያላት በአት (የጸሎት ቦታ) ነበረችውና፣ ሰይጣን በአንዷ በር ሲገባ ከጌታ የታዘዘ መልአክ አሮንን በአንዷ በር አስወጥቶ በሰይጣኑ በሩን ዘግቶ ዋሻውን ደፍኖ ታላቅ ድንጋይን ጫነበት፣ አሮንም ውሃ የሚቀዳባቸው (4) እንስራዎችን በአንበሳ እየጫነ ለገዳሙ በመውሰድ አንበሳው (ለ10) ዓመት ያህል ውሃ እየቀዳ ሲያገለግለው ኖረ (የግንቦት 21 ቀን መጽሐፈ ስንክሳር)::

## ሰይጣን ድንጋይን ስለ መሸከሙ

(ታሪክ) ከሕሙማን አጋንንትን የማውጣት መንፈሳዊ ሀብት የተሰጠው ሚልኪ የሚባል የግብፅ ባሕታዊ (14) ሰዎች ማንቀሳቀስ የማይችሉትን ድንጋይ ለገዳሙ መነኮሳት የሚያገለግሉ ገንዳዎችን (የእንስሳት ውሃ መጠጫዎችን) በደንጊያው ብስ ውስጥ በሰይጣን አንገት ላይ አሸክሞ ከሮም ወደ ግብጽ አገር ልዩ ስሟ ጡር ወደ ምትባል ገዳሙ እንዲያደርስ ያደርግ ነበር (የመስከረም አንድ ቀን መጽሐፈ ስንክሳር):: ጌታ፣ አጋንንትን አውጡ ማቴ.10.8፣ እባቡንና ጊንጡን ብትረግጡም የጠላት (የዲያብሎስ) ኃይል ሁሉ ምንም ሲጎዳችሁ አይችልም በማለት፣ መንፈሳዊ ሥልጣንን እንደሰጣቸው፣ እነሱም አጋንንት እንደተገዙላቸው የተናገሩት (12ቱ) ሐዋርያት እና (70ው) አገልጋዮች፣ ሉቃ.10.16-21፣9.1-7. ልበአምላክ በተባለው በንጉሥ ዳዊት ላይም አድሮ መዝ.88.18-21፣ የሐዋ.13.21-23

(37) የጌታ መስቀል፣ በንግሥት ዕሌኒ ከወጣ በኋላ ዳግመኛ መቼ እና በማን ተቀበረ? →



በተኵላና በእባብ ላይ ትጫማለህ፣ አንበሳንና ዘንዶንም ትረግጣለህ (በአራዊት ሁሉ ላይ ትሰለጥናለህ) ያመነም ሁሉ ይፈጸምለታል ብሎ እንደተናገረ፣ መዝ.90.13-16. እንዲሁም ጌታን ተስፋ አድርገው በአንበሳ ጉድጓድ ተጥለው እና ከአንበሳ አፍ ድነው፣ አንበሳ እንደተገዛላቸው እንደነ ዳንኤል ሁሉ ዳን.6.16-28፣ ዕብ.11.32-35 አሮንና ሚልኪ የሚባሉ ቅዱሳን በእምነታቸውና በበጎ ሥራቸው ሰይጣንንና አንበሳን ገዝተዋል::

ጀ፴- 140 በገነተ ፍቅርኪ ማርያም አስካለ ትእምርት ተረክበ፣
ፍሬ ስብሐትኪ ፍድፉድ እስከ በኀቤሁ ተመክዐበ፣
ዘዘዚአሁ ጣዕሙ ጸገየ ሕንባበ፣
ወዘዘዚአሁ ፄናሁ ዘይሰልብ አልባበ፣
ልሳነ ዕፍረት ጊዮርጊስ መዓዛ ወሀበ::

ማርያም ሆይ በፍቅርሽ የተክል ቦታ፣ የምልክት ፍሬ ተገኘ የክብርሽ ፍሬም፣ ጣዕሙና መዓዛው የየራሱ የሆነ፣ ልብን የሚመስጥ አበባን አፍርቶ በእርሱ ዘንድ እጽፍ ድርብ እስከሚሆን ድረስ በዛ ልሳነ ዕፍረት (ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ፍጹም አምላክ መሆኑን በፍጹምነት መስክሮ መዓዛ ጸሎቱ የተወደደለት) ጊዮርጊስም መዓዛን ሰጠ (መዓዛ ረድኤትን አገኘ)::

## እመቤታችን በርግብ አምሳል በጊዮርጊስ ቤት

(ታሪክ) ስለ እግዚአብሔር ወልድ አምላክነት፣ ምስክርነቱን የማያቋርጥ ጊዮርጊስ የሚባል ጻድቅ ሰው ነበር በዚህ ምክንያት የአገሪቱ መኳንንት ለብዙ ዘመን በጽኑ እስራት ፈረዱበት ጽኑ ከሆነ ፍርድና እስራት የተነሣም የራስ ሕመም ነበረበት፣ ከዕለታት አንድ ቀንም (ግንቦት 11 ቀን) ተኝቶ ሳለ ከሌሊቱ (በ11) ሰዓት እመቤታችን በነጭ ርግብ አምሳል ሆና ወደቤቱ ገብታ ክንፎችዋን በላዩ ላይ ዘረጋች በዚያን ጊዜም ከእንቅልፉ ነቅቶ እጆቹን አንሥቶ የርግቧን ክንፍ ያዘ፣ ወዲያውም ተፈወሰ ቤቱንም መዓዛ ሞላው እመቤታችንም በረድኤት እንደጎበኘችው አወቀና ደስ ከሚያሰኝ ከእመቤታችን መዓዛ ጣዕም የተነሣ (ለ4) ቀን ያህል ሳይበላና

(38) የጌታ መስቀል፣ በንግሥት ዕሌኒ አማካኝነት በኢየሩሳሌም ቤተመዛግብት ከኖረ (ከ287) ዓመት በኋላ (በ614) ዓ.ም ኪርዮስ (ፎቃ) በተባለ በፋርስ ገዥ ተወስዶ በፋርስ ተቀበረ፣ (የመጋቢት 10 ቀን መጽሐፈ ስንክሳር እና የተለያዩ የታሪክ መጻሕፍት)::

www.ethiopianorthodox.org

ሳይጠጣ ቆይቶ የእመቤታችን መዓዛ ረድኤት እንደ ምግብና እንደ መጠጥ ሆኖት ደስ ተሰኝቷል (221 ተአምረ ማርያም)::

ጀ፻፵፩፦141 በሠላስ አዕባን ገጸ ሥላሴሁ ለአምሮ፣
ሐኒጸ ቤትኪ ድንግል ድኅረ ፈጸመ ሣርሮ፣
አመ ወረደ ለበዓል ምስሌኪ በአማኅብሮ፣
እንዘ ይብላ ቃለ ለዘምሮ (በዘምሮ)፣
ልዑል ቀደሰ ማኅደሮ ደናግል ለጽጌኪ ዘበጣ ከበሮ::

*ድንግል ሆይ አባትሽ ዳዊት ልዑል እግዚአብሔር ማደሪያው የሆንሽ አንቺን ቀደሰ (ልዩ አደረገ) ብሎ እንደመሰከረ ሁሉ መዝ.45.4 ልጅሽ የሦስትነቱን አካል ለመግለጽ በሦስት ድንጋዮች ቤትሽን ሠርቶ ከፈጸመ በኋላ በአንድነት ከአንቺ ጋር ለበዓል በወረደ ጊዜ ደናግል፣ ልዑል እግዚአብሔር ማደሪያው የሆንሽ አንቺን በንጽሕና፣ በቅድስና አከበረ እያሉ፣ በቃል ለመዘመር ለልጅሽ ከበሮን መቱ፣ (በቃል በመዘመር ምስጋናን አቀረቡ)::*

(ሐተታ) ጌታ፣ በሦስት ድንጋዮች ብቻ አንዲት ቤተክርስቲያንን መሥራቱ፣ ከላይ በትርጉሙ ላይ እንደተመለከትነው በስም፣ በአካል፣ በግብር ሦስት፣ በመለኮታዊ ሥልጣን፣ በህልውና አንድ አምላክ የመሆኑን ምሥጢር ለመግለጽ እና ዘፍ.1.26-28፣ ማቴ.28.18-20. ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት፣ አምስት እንጀራንና ሁለት ዓሣን ብቻ፣ ባርኮ 5,000 ሰዎችን መግቦ ተአምሩን እንደአሳየ ሁሉ፣ ዮሐ.6.9-15. ከዐረገ በኋላም፣ ልዩ ተአምሩን ሠርቶ ለማሳየት ነው:: እንዲሁም ድንጋይ፣ በባሕርዩ በክረምት አይለወጥም፣ በበጋም አይሰነጠቅም ቋሚ እና ኗሪ ነው:: የእኔ ባሕርይም አይለወጥምና፣ ለዘለዓለም የምኖር እኔ አምላካችሁ ቋሚ እና ኗሪ ሥራን ሠራሁላችሁ ለማለት! ቅዱስ ጴጥሮስንም አንተ የሃይማኖት መሠረት ነህና፣ በአንተ መሠረትነት ቤተክርስቲያኔን አንጻታለሁ (ምእመናንን በሃይማኖት አንጽባታለሁ) ብሎ እንደተናገረ

(39) ኪርዮስ፣ (ፎቃ) የተባለ የፋርስ ሀገረ ገዥ ወስዶ የቀበረው የጌታ መስቀል፣ መቼና በማን ተመለሰ? →



ማቴ.16.18-20. ዘለዓለማዊ ክብርን የምታሰጥ ቤተክርስቲያን የሃይማኖት መሠረት በሆኑ በሐዋርያት አማካኝነት እመቤታች በዐረገች (በ4) ዓመት (በ53) ዓ.ም ፊልጵስዩስ በምትባል አገር፣ (ሰ 20 እና ሰኔ 21) ቀን የመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያንን (በ3) ድንጋ ብቻ ሠራ:: (43) ዓመት ሙሉ የታነጸው እና ቁመቱ 5.433 ክን ከሁለት ስንዝር የነበረው የክፉ ሰዎች ግንብ ግን፣ በአንዲት ቃ በነፋስ ተበተነ ዘፍ.11.1-10፣ መጽ.ኩፋ.10.10-22::

## ቤተክርስቲያን ለመጀመሪያ ጊዜ በየት ተሠራች?

(ታሪክ) እመቤታችን ባረገች (በ4) ዓመት (በ53 ዓ.ም) ለመጀመሪ ጊዜ የእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን ፊልጵስዩስ በምትባል አገር ያ ዕንጨት፣ ያለ ሣር፣ ያለ ውኃና ያለ ጭቃ «በ3» ድንጋዮች ብ በተወደደ በልጅዋ ፈቃድ ተሠራች የቤተ ክርስቲያኒቱ ሕንፃ ተጀም እስከ ተፈጸመ ድረስም ድንጋዮች በሐዋርያት እጅ ውስ ይለመልሙ ነበር፣ ሕንጻውም (ሰኔ 20 ቀን ተፈጽሞ በነጋው ሰ 21 ቀን) ጌታ ራሱ ቀድሶ ሥጋውንና ደሙን ለሐዋርያት አቀብሎ በታላቅ ክብር ወደ ሰማይ ዐርጓል:: (የሰኔ 20 እና 21 ቀን መጽሐ ስንክሳር፣ እንዲሁም 99 ተአምረ ማርያም)::

፻፵፪፦፦142 ዑርኤል (ሱራኤል) ለሄኖክ ዘአርአዮ፣
ትእምርተ አምሳልኪ ቤተ ነድ፣
ዘመብረቅ ጠፈራ ወኀብራ በረድ፣
በከመ ተነበይኪ ድንግል ጽጌ ነጐድጓድ፣
ያስተበፅዑኒ ኵሉ ትውልድ፣
ወእምኔሆሙ አንሰ ገብርኪ ዋሕድ::

የነጐድጓድ አበባ (የብርሃን እናት) የሆንሽ ድንግል ሆይ ዑርኤል (ሱራኤል) የሚባል መልአክ ለሄኖክ ያሳየው ጣራዋ መብረቅ፣ መልኳ በረድን የሚመስልና የእሳት አዳራሽ የሆነች ቤት የምሳሌሽ

(40) የጌታ መስቀል፣ በፋርስ ሀገር ከተቀበረ (ከ14) ዓመት በኋላ (በ628) ዓ.ም ህርቃ በተባለ በሮም ንጉሥ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ (የመጋቢት 10 ቀን መጽሐፈ ስንክሳ እና የተለያዩ የታሪክ መጻሕፍት)::

www.ethiopianorthodox.org

ምልክት ናት (ሄኖ 4.45-51 የሐምሌ 21 ቀን መጽሐፈ ስንክሳር) ቀድሞ ንጉሥ ሰሎሞን ንግሥታት እንደሚያመሰግኑሽ፣ መኃ. 6፡ 9-10 አንቺም ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል ብለሽ እንደተናገርሽ ሉቃ.1.35-50 ከእነርሱም አንዱ እኔ ባሪያሽ አመሰግንሻለሁ:: (ይህ ታሪክ እመቤታችን) (በ48) ዓ.ም ገደማ የካቲት (16) ቀን ጎልጎታ በምትባል ቦታ በጌታ መቃብር ጥግ ስትጸልይ ልጇና ፈጣሪዋ ቃል ኪዳን በገባላት ጊዜ በእሳት አጥር የተሠራችውንና ያሳያትን ቤት ቀድሞ ሄኖክ ካያት ከእሳት አዳራሽ ጋር የሚያነጻጽር ነው)::

## በዓለም የመጀመሪያው ጸሐፊ ማን ነበር?

ሄኖክ ዓለም በተፈጠረ (በ1121) ዓመት ከአባቱ ከያሬድና ከእናቱ ከባረካ ተወለደ ሄኖክ ማለት አዲስ ማለት ነው ሄኖክ የነፋሳትን መውጫና የከዋክብትን መነሻ መድረሻ ያወቀና ብዙ ራእዮችን ያየ ጌታ የመረጠው ሲሆን፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የጌታን ቃል የጻፈና ጽሑፍን ለትውልድ (ለልጅ ልጁ ለኖህ) በጽሑፍ እንዲተላለፍ ያደረገና ኩፋ 5.22-25 ሄኖ.18.42. በገነት ጥግ (፮) ዓመት ጌታን ሲያገለግል ኖሮ (በ7ተኛው) ዓመት፣ ዓለም በተፈጠረ (በ1486) ዓመት በዚህ ዓለምም (365) ዓመት ኖሮ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሞት የተሠወረ የጌታ ባለሟል ነው ዘፍ.5.23-24፣ ኩፋ.5.20:: በመጨረሻው ሰዓትም የባሕር አውሬ የተባለው ሐሳዊ መሢሕ ይመጣል ተብሎ ትንቢት እንደተነገረ ዳን 7፡ 3-21 ሐሳዊ መሢሕ፣ የሐሰት ተአምርን በማድረግና እኔ ክርስቶስ ነኝ በማለት ብዙዎችን በሚያስትበት ጊዜ ከነቢዩ ኤልያስ ጋር ሆኖ ሐሳዊ መሢሕ አምላክ አይደለም፣ ፍጥረታትን ሁሉ የፈጠረ አምላክ አለ ብለው (1260) ቀን ሲያስተምሩ ሁለቱንም፣ ያስገድላቸዋል፣ እነሱም በሰማዕትነት ያርፋሉ ራእ.11.1-14::

፪፻፲፫:-143 እመ ዐረጉ አድባረ ወወረድኩ ገዳመ፣
ኅጣእኩ ጽጌ ዘይመስለኪ ፍጹመ፣
ከመ እስብሕ ዳግመ ተአምረኪ መድምመ፣

(41) መስቀል፣ በዕለተ ምጽአት ጊዜ ምን አገልግሎት ይሰጣል? →



አሰምዕኒ ድንግል ማኅሌተ ሕጻናት ጥዑመ፣
ወበየማንኪ ክፍልኒ ቀዊመ::

*ድንግል ሆይ ወደ ተራሮች ብወጣና ወደ በረሃ ብወርድ በንጽሕና፣ በቅድስና አንቺን የሚመስል ፈጽሞ አጣሁ አስደናቂ የሆነ ተአምርሽንም አመሰግን ዘንድ ደስ የሚያሰኝ የሕጻናት ማኅሌትን (ምስጋናን) አሰሚኝ፣ በቀኝሽ መቆምንም አድዪኝ::*

## እመቤታችንን የሕጻናት ምስጋናን አሰሚኝ ስለምን አለ?

እመቤታችንን ደስ የሚያሰኝ የሕጻናት ምስጋናን አሰሚኝ ማለቱ፣ መላእክት በነገድ በነገድ ሆነው ጌታን በዜማ እንደሚያመሰግኑና ከ144,000 (ከመቶ አርባ አራት ሺህ) ሕጻናት በቀር ያቺን ምስጋና (ሰማያዊ ማኅሌትን) ማወቅ ለማንም አልተቻለውም ተብሎ እንደተጻፈ ሄሮድስ ያስገደላቸው ሕጻናት ጌታን በዜማ ያመሰግናሉና ራእ.14.3-6 ቂም በቀል እንደሌላቸው እንደ ሕጻናት ካልሆኑም ከሕጻናት መዓርግ መድረስ እና መንግሥተ ሰማያትን መውረስ አይቻልም ማቴ.18.3:: ከመዓርጋቸው ካልደረሱም ምስጋናቸውን ማመስገን አይቻልምና፣ ጌታ በተወለደ ጊዜም እረኞች ከመላእክት ጋር፣ ሉቃ.2.13. በሆሣዕና ጊዜም ሕጻናት ደስ የሚያሰኝ ምስጋናን አቅርበዋልና:: በተያያዘ ምሥጢርም ከሕጻናትና ጡት ከሚጠቡ ልጆች አፍ ምስጋናን አዘጋጀህ የሚል አማናዊ ትንቢት በሕጻናት አንደበት ተፈጽሟልና:: ደቂቅ የሚላቸውም (የ40 እና የ80 ቀን) ሕጻናት ሲሆኑ፣ ሕጻናት የሚላቸው ደግሞ የዓመት እና የ2 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ናቸው መዝ.8.2 ንባብና ትርጓሜው::

## ጌታ የባረካቸው ሕጻናት ምን ሆኑ?

(ታሪክ) ከዕለታት አንድ ቀን ከጌታ ሊያስባርኩ ወላጆቻቸው ሕጻናትን ሲያመጡ ሐዋርያት ሕጻናቱ ይጠቀጥቁናል፣ ትምህርትም ያስፈቱናል ብለው

(42) ከሰማይ ሥጋን ይዞ ያልወረደ ጌታ፣ ከድንግል ማርያም የነሣውን ሥጋ፣ በመስቀል ላይ ሠውቶ ዓለምን እንደ አዳነ ሁሉ፣ ዳግመኛ ለፍርድ ሲመጣ በጦር የወጉት አይሁድ በዓይን እያዩት በመስቀል ላይ ሆኖ ለሁሉም እንደየሥራው ይከፍላል ራእ.1.7፣ 2ኛ.ተሰ.1.6-10::

www.ethiopianorthodox.org

ቢቈጡ ጌታ ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ሕጻናትን ተዉአቸው አትከልክሏቸው ወንጌል የምትነገርና መንግሥተ ሰማያት የምትሰጥ ቂም በቀል እንደሌላቸው እንደነዚህ ላሉ ነውና ብሎ በእጁ የባረካቸው የጌታ ባለሟሎች ናቸው ማቴ.19.13-16. የእነዚህ ሕጻናት ቍጥርም (ከ200) በላይ ሲሆን፣ ከዲቁና እስከ ጵጵስና ያልደረሰም የለም ከእነዚህም አንዱ አግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ ነው:: ታሪኩም ይቀጥላል::

## ጌታ የታቀፈው ሕጻን ስሙ ማነው?

(ታሪክ) አግናጥዮስ የሐዋርያው የዮሐንስ ደቀ መዝሙር የነበረ ሲሆን፣ ታሪኩ በማቴዎስ ወንጌል 18:1-5. እንደተጻፈ ጌታ አንድን ሕጻን ጠርቶ በእጁ እያመለከተና ሕጻኑን በፊቱ አቁሞ እንደዚህ ሕጻን ካልሆናችሁ እና ካልተመለሳችሁ መንግሥተ ሰማያትን አትወርሱም ካላቸው ሕጻናት ውስጥ አንዱ ሕጻን አግናጥዮስ እንደነበረ ሊቃውንት ይናገራሉ።አግናጥዮስም የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳስ ሆኖ ሲያስተምር አሕዛብ ለሁለት አንበሶች ሰጥተውት (በ117) ዓ.ም ገደማ ታኅሣሥ (24) ቀን በሰማዕትነት ያረፈ የክርስቶስ አገልጋይ ሲሆን አግናጥዮስ ምጥው ለአንበሳ ይባላል፣ ይህም ማለት ለአንበሳ የተሰጠ (የተጣለ) ማለት ነው (የታኅሣሥ 24 ቀን መጽሐፈ ስንክሳር፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ እና የቤተክርስቲያን ታሪክ በሉሌ መልአኩ)::

፻፵፬፦144 ይበርቅ ሥንኪ እምሥነ ጽጌያት ወአዕናቍ፣
እስመ ወለድኪ ፀሐየ በወርኀ ፍሥሓ ኵርያቍ፣
መርዓተ ሰማይ ማርያም ክብርተ ሥዕርት (ክብርተ መሥዕርት) እምሕቍ
ኢትኅድግኒ ለገብርኪ እስከ እነግር በኀሕቍ፣
ተአምረኪ ዘይበዝኀ እምኍልቍ::

*ከከበረ እና ከተወደደ ዞጲ ከሚባል ዕንጨት ይልቅ የምትከብሪ (ክብርሽ ከራስ ጸጉር የሚበዛ) የሰማይ እመቤት ማርያም ሆይ ከአበባዎች እና ከዕንቍዎች መልክ ይልቅ፣ መዓዛ ረድኤትሽ ይበልጣል የደስታ ወራት በሆነ በታኅሣሥ ወር ፀሐይ ክርስቶስን ወልደሻልና:: አባትሽ ዳዊት፣*

(43) ከቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ፣ ቀድሞ የተጻፈው መጽሐፍ ማነው? →

www.ethiopianorthodox.org



*እስካረጅና እስከሸመግል ድረስ፣ ክንድህን (ሥልጣንህን)፣ ቸርነት ለሚመጣው ትውልድ እስክነግር ድረስም አቤቱ አምላኬ ሆይ አትተ ብሎ እንደጸለየ መዝ.70.17-19. ከቍጥር የሚበዛ ተአምርሽን በእር ዘመኔ እስክነግር ድረስ ባሪያሽን አትተዪኝ::*

፻፵፭፦145 ተአምረ ፍቅርኪ ማርያም ለኅሊና ልብየ ሆኮ፣
ወአስተናሥአ ይበልኪ ኮለ ሐይቅ ዘኢያረኮ፣
ከመ ዔና ገዳም ጥንቁቅ (ጥንቁቀ) እግዚአብሔር ዘባረኮ፣
ለልብስኪ ወርቅ ዘኅብረ ወይን አጼኑ ሰሊኮ፣
ታሕተ ጽላሎትኪ ንግሥት ክፍልኒ አስምኮ::

*የሰማይና የምድር ንግሥት ማርያም ሆይ የፍቅርሽ ተአምር ልቤ ቀሰቀሰው፣ ልዩ እንደሆነ እንደበረሃ መዓዛ አድርጎ እግዚአብ (ቢልዩ ጥበቡ ፈጽሞ ደስ የሚያሰኝ አድርጎ) እንደፈጠረውና እ ባረከው የኢያሪኮ የባሕር ዙሪያ ዕንኮይ ነሽ ይልሽም ዘንድ አነሳሳ የወይን መልክ ያለው የወርቅ ልብስሽንም መዓዛ አሸት ዘ ከረድኤትሽ ጥላ አሳርፊኝ (መዓዛ ቅድስናሽን እነግር ዘ አድርጊኝ)::*

(ሐተታ) እመቤታችንን በዕንኮይ መመሰሉ፣ ስለምንድነው ቢሉ ዕን ፍሬው ክብ ሲሆን ቅጠሉን አህዮች፣ አበባውን ንቦች፣ ፍሬውን እረኛ ይወዱታል ከእመቤታችን የተገኘ፣ በአበባና በፍሬ የተመሰለ ጌታም እ ንብ ያለ ሩካቤ (ያለግንኙነት) በቃል ብቻ በማሕፀኗ ማደሩን ለማስረ ነው በወለደችው ጊዜም እንስሳት (አህያና ላም) ፈጣሪያቸው መሆ አውቀው ሰግደው ትንፋሻቸውን ገብረውለታል፤ እረኞች አመስግነውታልና ነው (የታኅሣሥ 29 ቀን መጽሐፈ ስንክሳር፣ 62 213 ተአምረ ማርያም)::

፻፵፮፦146 ከመ ዔና ልብስኪ ወዔና አንፍኪ ወመዓዛ አፉኪ በነ
እምነ ጽጌያት ዘገነት ወበውስተ ገዳም ዘይጼኑ፣
ተአምረ ቍርባን ማርያም ለኪሩብ ጢሰ ዕጣኑ፣
ማየ ልብንኑ ሰሊሆትኑ፣
መዓዛ ፍቅርኪ ዘይመስል መኑ::

*ኪሩብ የሚባል መልአክ ለሚያቀርባት የዕጣን ጢስ ምሳሌ የሆ ማርያም ሆይ ራእ.8.3-4. በገነትና በበረሃ ደስ የሚያሰኝ መዓዛ*

(44) ከቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ፣ ቀድሞ የተጻፈው መጽሐፈ ሄኖክ ሲሆን፣ ይህም ዓለም በተፈ ... የሰሎሞን እና የሲራክ መጻሕፍት፣ የትርጓሜ መግቢያ)::

ከአላቸው አበባዎች ይልቅ በንጽሕና፣ በቅድስና እንደ ተሸለመ እንደ አካልሽ መዓዛ ሁሉ የሚሆን በእውነት አለን? የነጭ ዕጣንና የልባንጃ ውሃ ነውን? ወይስ ሰሊሆት የተባለ ሽቱ? የፍቅርሽን መዓዛስ የሚመስል ማነው?

ፀ፻፵፯፦147 ሥርጋዌ ሰማይ ትእምርተ ዓመታት ፀሐይ ወወርኀ ወከዋክብት፣
ወሥርጋዌ ምድር ጽጌያት፣
የኀልፉ ግብተ ከመ ጽላሎት፣
ለኪሰ ማርያም ንግሥት፣
ኢየኀልፍ ለዓለም ሠርጐኪ ስብሐት::

የሰማይና የምድር ንግሥት የሆንሽ ማርያም ሆይ ሰማይ የተሸለመባቸው የዘመናት ምልክቶች የሆኑ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት፣ ምድር የተሸለመችባቸው አበባዎች ዘፍ.1.10-20 ድንገት እንደ ጥላ ያልፋሉ (ይጠፋሉ) ዕዝ.ሱቱ.5. 39-43፣ ማቴ 24. 29-36 ለአንቺ የሚቀርበው ምስጋና ግን ነቢዩ ኢሳይያስ አንቺን በኢየሩሳሌም መስሎ እንደተናገረልሽ ለዘለዓለም አያልፍም (አይጠፋም) ኢሳ.60.20-21::

ፀ፻፵፰:-148 ተአምርኪ ማርያም ሶበ ተጽሕፈ በበአሐዱ፣
ዓለም ጥቀ እምኢያግመሮ ለከበዱ፣
ይትፌሣሕ ቦቱ ወይትሐሠይ ከመ ልማዱ፣
አንብሪ ጽጌ አፉየ ለሕጻንኪ በእዱ፣
እስመ ተላህዮ በጽጌ ለሕጻን መፍቅዱ::

ማርያም ሆይ የልጅሽ ተአምር እያንዳንዱ ቢጻፍ ኖሮ ዓለም እንደማይችለው ሁሉ ዮሐ.21.24-25 ተአምርሽም ሁሉ እየአንዳንዱ ቢጻፍ ዓለም እንኳን ክብደቱን ፈጽሞ ባልቻለውም ነበር ሁል ጊዜ እንደሚያደርገው በሱ ፈጽሞ ደስ ይለው ዘንድ ከአንደበቴ የተገኘውንና ደስ የሚያሰኝ ምስጋናን በልጅሽ እጅ ላይ አኑሪ፣ በአበባ መጫወት ለሕጻን ፍላጎቱ (ነጭና ቀይ መልክ፣ ባለው አበባ)

---

(45) ሶምሶን፣ በአንድ አጥንት ሺህ ሰው የገደለ ስንት ጊዜ ወርውሮ (ስንት ጊዜ መትቶ) ነው? ⟶



ለተመሰለ ልጅሽ ማለትም በመለኮቱ ነጭ፣ በሰውነቱ ቀይ ለተ ልጅሽ) መኃ. 5.10 ከቂም ከበቀል ንጹሕ የሆነ ጸሎትን መቀ ፈቃዱ ነውና::

ፀ፻፵፱፦149 አኮ ዘሐይቅ ጽጌረዳ ወዘባሕር ሰግላጠ፣
ዘአቅረብኩ ለኪ አምኃ ተአምር ሥሉጠ፣
መፍቀሪተ ሰብእ (መፍቀሪተ ፍቅር) ማርያም እንተ አልብኪ ተውላጠ፣
ጽጌ ልሳንየ አስተባዝኂ ኅዳጠ፣
ወረስዩ በአንፍኪ ዔናሁ ስውጠ::

መለወጥ (በደል) የሌለብሽና ሰውን የምትወጂ፣ የሰላም እመ ማርያም ሆይ ያቀረብኩልሽ የተአምር እጅ መንሻ በሙሉ የባ ዙሪያ ጽጌረዳና ከባሕር ማዶ የመጣ ሽቱ አይደለምና፣ ጥቂት የ የአንደበቴን ምስጋና አብዢ፣ መዓዛውንም በአፍንጫሽ (በአ ዘንድ) የተወደደ አድርጊ::

ፀ፻፶:-150 አባእኩ ለኪ ስብሐተ ተአምር ዘይሤለስ በበሃምሳ፣
ህየንተ ጽጌያት ሃምሳ ለሥዕልኪ አክሊለ ርእሳ፣
ተወኪፈኪ ማርያም አንጽሕኒ እምአበሳ፣
ከመ አንጻሕኪያ ለግብጻዊት እምርኩሳ፣
እስከ መቃብሪራ ከረየ ዘይጥህር አንበሳ::

ማርያም ሆይ ለሥዕልሽ የራስ ዘውድ (የምስጋና ምሳሌ) በሆ በአምሳ አበባዎች ፈንታ በሦስት አምሳ የተከፈለና ድንቅ ተአ ያለበት ምስጋናን አቀረብኩልሽ፣ የሚያገሳ አንበሳ መቃብሯን እ ቆፈረላት ድረስም ግብጻዊት ማርያምን ከበደሏ እንዳነጻሻት ይ ምስጋና ተቀብለሽ ከበደሌ ንጹሕ አድርጊኝ:: (የ50ው) የጽጌረዳ አስደናቂ ሙሉ ታሪክን በክፍል አንድ መጽሐፍ፣ ከገጽ 24-27 ይመልከቱ::

## አንበሳ መቃብሯን ስለ ቆፈረላት ደሃ

(ታሪክ) በ5ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መንፈሳዊት አርበኛ እንደተነሳች የተለያዩ የታሪክ መጻሕፍት የመሰከሩላት እና በግ በረሃ ብዙ ጊዜ በመኖሯ፣ ግብጻዊት ማርያም ተብላ የምትጠራ ሴት ከተወለደች (ከ12) ዓመት ጀምሮ ሰይጣን ስለ ዝሙት ፍቅር

---

(46) የሰው ዐፅም፣ ክቡር ነውና፣ የአዳምን ዐፅም ልጆቹ በክብር ቀበሩ፣ ዕጣንም እ መጽሐፈ ስንክሳር)::

www.ethiopianorthodox.org

ያለዋጋ ሥጋዋን እስከ መስጠት አደረሳት፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ግን ከጌታ መቃብር ሊባረኩ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ የሚሹ ምእመናንን ኄታ ገልጸላት ከእነሱ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ትሔድ ዘንድ ልቧ ተነሳሥቶ በመርከብ ተሳፈረች ባለ መርከቦችም የመርከብ ዋጋን በጠየቋት ጊዜ ስለ መርከብ ዋጋ ያመነዝሩባት ዘንድ ፈቀደችላቸው፣ ኢየሩሳሌም እስክትደርስ ድረስም ይህን ክፉ ሥራ አልተወችም፤ ወደ ቤተክርስቲያን ልትገባ ስትልም የእግዚአብሔር ኃይል ከለከላት ከዚህ በኋላ ስለ ኃጢአቷ አስባ ወደ ፈጣሪዋ ዓይነ ልቡናዋን አቅንታ እያለቀሰች ሳለች፣ የእመቤታችንን ሥዕል አይታ አለቀሰች፣ በዚህም ጊዜ ማርያም ሆይ ከዮርዳኖስ በረሃ ብትገቢ ሕይወትን ታገኛለሽ የሚል ቃል ከእመቤታችን ሥዕል ተሰማ ግብጻዊት ማርያምም ይህን ቃል ተቀብላ (እጅግ ደስ ብሏት) ወዲያውኑ ወጣች የዮርዳኖስንም ወንዝ ተሻግራ ጽኑዕ ተጋድሎን እየተጋደለች በበረሃ ውስጥ (47) ዓመት ኖረች፣ ይህ ዓመት ሲፈጸምም እንደገዳሙ ልማድ (40) ጾምን (ሁዳዴ ጾምን) በሱባዔ ሲፈጽም ዞሲማስ (ዞሲማስ) የሚባል ካህን ወደዚያች በረሃ በመጣ ጊዜ የጌታን ሥጋውንና ደሙን ያመጣላት ዘንድ ለመነችው፣ እርሱም እንዳለችው አመጣላትና ተቀበለች በ2ኛው ዓመትም እንደዚሁ እንዲያመጣላት ለመነችውና ይዞላት ሲሄድ፣ ዐርፋ አገኛት፡፡ አዳም ሆይ አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ በተባለው አምላካዊ ቃል መሠረት ዘፍ.2.7. ደኃዪቱ ግብጻዊት ማርያምን ከተፈጠረችባት መሬት ውስጥ ዘፍ.2.7፣ 3.19-20. ቅበራት የሚል ጽሑፍ ከራስጌዋ ካገኘ በኋላ ከበታቿ አንበሳ አስከሬኗን ሲጠብቅና በጥፍሮቹ ምድሩን (መቃብሯን) ሲቆፍር አይቶ፣ እጅግ አደነቀና በአስከሬኗ ላይ እንደ

አገሩ ሥርዓት ጸሎተ ፍትሐት አድርሶ አንበሳው በቆፈረላት ጉድጓድ በክብር ቀብሯታል፡፡ የግብጻዊት ማርያም ሙሉ ዕድሜዋ (85) ዓመት ሲሆን (12) ዓመት በልጅነት ያለ ኃጢአት፣ (26) ዓመት በዝሙት፣ (47)

(47) በጥፋት ውሃ ጊዜ ኖህ፣ የአዳምን ዐፅም በመርከብ ውስጥ አስቀምጦ ዕጣን ያጥን ነበር (የሚያዝያ 6 ቀን መጽሐፈ ስንክሳር)፡፡

www.ethiopianorthodox.org



ዓመት በጾምና በጸሎት ተወስና ኖራ ሚያዝያ (6) ቀን ዐረፈች (የሚያዝያ 6 ቀን መጽሐፈ ስንክሳር እና የተለያዩ የታሪክ መጻሕፍት)፡፡

፻፶፩፦151 ለምንት ሊተ ኢትበሊ እምአፈ ኃጥእ ውዳሴ ፣
ይበቊዐኒ ዘብየ እምአፈ ጻድቃን ቅዳሴ ፣
ጽጌ መድኃኒት ማርያም ዘሠረጽኪ እምሥርወ እሴ፣
እመ ተወከፍኪ ኪያየ አባሴ ፣
ተአምረኪ የአኵት ብናሴ፡፡

*ከእሴይ ዘር የተገኘሽ የሕይወት አበባ ማርያም ሆይ ከጻድቃን የሚቀርብልኝ ምስጋና ይበቃኛል፤ ከኃጥእ እንደበት የሚቀርብ ምስጋናን ግን አልቀበልም አትበዪ፣ በደለኛ የሆንኩ እኔን ብትቀበዪ ተአምርሽን ጨረቃ ያመሰግናል፣ (መላእክት፤ ሰማይና ምድር) ያመሰግናሉ፡፡*

፻፶፪፦152 መኑ ጽጌ ሐና አፈወ ውዳሴኪ ዘአረረ፣
ወመኑ ዘጸግበ ገቢሮ ድራረ፣
ተአምረኪ ኅብስተ ወስብሐተኪ መዓረ፣
ረስዪ ንስቲተ ንባብየ ውስተ አፈ ኵሉ ሦከረ፣
ዘይፌውስ ደዌ ወያነጽሕ ነውረ፡፡

*የሐና አበባዋ (ደስታዋ) የሆንሽ ማርያም ሆይ ሽቱ ምስጋናሽን የሰበሰበ ማነው? ተአምርሽን እንጀራ፤ ምስጋናሽንም ማር እንደ እራት አድርጎ የጠገበስ ማነው? ጥቂት የሆነ ነገሬን በሰው ሁሉ እንደበት ለምስጋናሽ ደስ የሚያሰኝና ከደዌ የሚፈውስ፤ ከነውርም የሚያነጻ አድርጊልኝ፡፡*

፻፶፫፦153 ተአምራተኪ በኅልዮ ኅሊናትየ ተሰቅሉ፣
እስመ ፍቅርኪ ሠረፀ ለልብየ በማዕከሉ፣
ወበከናፍርየ ወጽአ ለአጽቀ ስብሐትኪ ሐመልማሉ፣
ማርያም ጸሐፊ ማኅሌትየ በጽጌሁ ወበቆጽሉ፣
እለ ነጸርዎ ለፊደሉ ያንብብዎ ኵሉ፡፡

(48) በጠቅላላ ስለ ሰው ዐፅም ክቡርነት እና በጥንቃቄ እንዲያርፍ የያዕቆብ እና የልጁ የዮሴፍ ዐፅማቸው፣ ወደ ከነዓን ሄዶ በክብር እንደተቀበረ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል ዘፍ.50.1-15፣ መጽ.ኢያ.24.32፣ዕብ 11፣ 22-23

ማርያም ሆይ ተአምሮችሽን በማሰብ ሐሳቦቼ ተንጠለጠሉ (ተመሰጡ) ፍቅርሽ በልቤ ውስጥ በቅኗልና የምስጋናሽም ቅርንጫፍ ቅጠሉ በከንፈሮቼ ለምልሟልና፣ ፊደሉን ያዩት ሁሉ ያነብቡት ዘንድ ምስጋናዬን በቅጠሉና በአበባው ጻፉ::

## ፊደል መቼና በማን መጣ? ፊደል ማለትስ ምን ማለት ነው?

(ሐተታ) ፊደል ማለት ሥዕል፣ መግለጫ፣ ዘር፣ ቀለም ማለት ሲሆን፣ ጌታ ፊደልን ለመጀመሪያ ጊዜ የገለጸለት ሄኖስ ለሚባለው ሰው ነው፣ ሄኖስ ማለትም መዓዛ፣ መሠረት፣ ፍጹም ሰው ማለት ነው፣ ፊደልን ከፈጣሪ የተቀበለም ዓለም በተፈጠረ (በ700) ዓመት ገደማ ነው ይህስ እንደምን ነው ቢሉ ከአቤል ጀምሮ እስከ ሄኖስ ድረስ የነበሩ ሰዎች የአቤል ደም ያጥፋን እያሉ ሲምሉ ቈይተዋል:: በኋላ ግን ሄኖስ ተመራምሮ መማል (ማመንና) በእግዚአብሔር ስም እንጂ በሰው ደም መማል (በሰው ማመን) አይገባም ብሎ የእግዚአብሐሬን ስም መጥራትና መማል ተጀመረ ዘፍ 4. 26:: በዚህ ጊዜም ጌታ (22ቱን) ፊደላት በሰማይ ሰሌዳ (በሰማይ ብራና) ጽፎ ለሄኖስ አሳየው፣ ፊደሎች (22) መሆናቸውም (የ22ቱ) ሥነ ፍጥረት ምሳሌ ስለሆኑ ነው ዘፍ 1.3-31:: ከአዳም ጀምሮ እስከ ያዕቆብ ድረስ ላሉ ለ22ቱ አርእስተ አበው ምሳሌ የሆኑ እኒህ (22ቱ) ፊደላትም፣ በመዝሙር (118). ከቍጥር (1). አሌፍ በሚል ቃል ተነሥተው፣ ታው በሚል ቃል የሚጨርሱ ሆነው፣ ለየአንዳንዳቸውም 8.8 ቍጥር ያላቸውና በጠቅላላ ግን (176) ቍጥርን ይዘው የሚገኙ ሲሆን፣ ሰቆቃወ ኤርምያስ በተባለው የመጽሐፍ ክፍልም፣ ከምዕራፍ (1) ቍጥር (1) ምዕራፍ (4) ቍጥር (22) ድረስ ተመላልሰው (በተደጋጋሚ) ተጽፈው ይገኛሉ::

(49) የኖህ ልጅ ሴምና መልከጼዴቅ፣ በእግዚአብሔር መልአክ እየተመሩ የአዳምን ዐፅም ወስደው የምድር መካከል በሆነች በኢየሩሳሌም አስቀመጡ መዝ.73.12-13 እና (የጥር ገድለ አዳም)::



## 22ቱ አርእስተ አበው የሚባሉ ማን ማን ናቸው?

(22ቱ) አርእስተ አበው (ከቀድሞ አባቶች ዋና ዋናዎቹ) የሚባ
ማን ማን ናቸው ቢሉ? ሊቀ ነቢያት ሙሴ ከኦሪት ዘፍጥረት እስ
ኦሪት ዘዳግም ያሉ አምስቱ የሕግ መጻሕፍትን ከመጻፉ በፊት
እግዚአብሔርን በሕገ ልቡና (በፍጹም እምነት) አምነው ይመ
ከነበሩት አባቶች በዋናነት የሚታወቁት በመጽሐፈ ኩፋሌ ምዕራ
(3) ከቍጥር (9) ላይ ከአዳም ጀምሮ እስከ ያዕቆብ ድረስ ያሉ
(22ቱ) አበው ብሎ ስማቸውን በዝርዝር ሳይጠራ፣ በጥቅ
የጠራቸውን (የ22) አባቶችን ስም ዝርዝርም ቅዱስ ሉቃ
በወንጌሉ፣ በምዕራፍ (3) ከቍጥር (34-38)

1. አዳም
2. ሴት
3. ሄኖስ
4. ቃይናን
5. መላልኤል
6. ያሬድ
7. ሄኖክ
8. ማቱሳላ
9. ላሜህ
10. ኖኅ
11. ሴም
12. አርፋክስድ
13. ሳላ
14. ዔቦር
15. ፋሌቅ
16. ራግው
17. ሴሩሕ (ሲሩሀ)
18. ናኮር
19. ታራ
20. አብርሃም
21. ይስሐቅ
22. ያዕቆብ በማለት በስም ገልጿቸዋል:: ቅዱስ ሉቃስ፣ እነዚህ
ሲጽፍም ቅዱስ ማቴዎስ፣ የጌታን ከሰማይ ወደ ምድ
የመውረዱንና ሰው የመሆኑን ምሥጢር ለመግለጽ
እስራኤል ዘሥጋ በተስፋ ተሰጥታቸው ወደነበረች ወደ ከነዓ
ዘፍ.12.12-21 የገቡ (በ42 ጊዜ) ጉዞ ነበርና፣ ኢያ.10.1-22.

(50) መጽሐፍ ቅዱስ ዕብ.7.1-4 እና ቅዱስ ያሬድ ድጓ በተባለ ድርሰቱ፣ መልከጼዴ
አባትና እናት የለውም ለምን አሉ? →

www.ethiopianorthodox.org

የዚህ (የ42) ጊዜ ጉዞን ከጌታ የትውልድ ሐረግ ጋር አነጻጽሮ ከአብርሃም እስከ ክርስቶስ ድረስ ያለው ትውልድ (42) መሆኑንና ጌታ በዚህ (በ42ኛው) ትውልድ መወለዱን ከላይ ወደታች እንደ ጻፈ ሳይሆን፣ ማቴ.1.18፣ የጥፋት ውሃ ከላይ ወደታች (ቍልቍል) የወረደው (በ7) አይነት፣ ከታች ወደላይ (ሽቅብ) የፈላውም (በ70) አይነት ነበርና፣ ዘፍ.7.11-13. የሰው የዕድሜ መጠኑ (70) ነው የተባለለት ሰውም መዝ.89.10. ከዚህ ዓለም በሞት ከመለየቱ በፊት የበደለውን ሰው (70) ጊዜ ይቅር ማለት ተገቢ የመሆኑን ምሥጢር፣ ማቴ.18.21-23፣ በጠቅላላም ጌታ የመጣ (በ77) ትውልድ ላይ የመጣውን ፍዳ መርገም ለማጥፋት እንደሆነ ለማስረዳት፣ ሥጋም አምላክ መሆኑንና የጌታ ዕርገቱን ሲመለከት፣ ከማቴዎስ የትውልድ አቈጣጠርና አጻጻፍ (ስለጌታ የትውልድ ሐረግ ከወንጌላውያኑ አገላለጽ) በተለየ መልኩ፣ የኤሊ ልጅ ብሎ ጀምሮ የእግዚአብሔር ልጅ ብሎ በሚጨርስ የትውልድ ሐረግ፣ (የ77) የትውልድ ሐረግን ከታች ወደላይ በመቍጠርና በመጻፍ ነው ሉቃ.3.23-38፡፡ የኤሊ ልጅ ከሚለው፣ የእግዚአብሔር ልጅ እስከሚለው ድረስ ቢቈጠርም፣ (77) ትውልድ ይሆናል፡፡ በዚህ በምዕራፍ (3) ከቍጥር (34) እስከ ቍጥር (38) ስንመለከት ደግሞ፣ ለዚህ ሁሉ ታሪክ መነሻ የሆኑ (የ22) አባቶችን ስም ዝርዝር ከላይ እንደተገለጸው እናገኛለን፡፡ በሉቃስ ወንጌል የተጻፈ ስም ዝርዝራቸውን ለማግኘትም፣ የቅዱስ ሉቃስ የትውልድ ሐረግ አቈጣጠርና አጻጻፍ፣ ከወንጌላውያኑ የተለየ መሆኑን ከላይ እንደተመለከትነው፣ ከታች ወደላይ ነውና፣ ከምዕራፍ (3) ከቍጥር (34) ጀምረው ይቍጠሩ፡፡ ቅዱስ ሉቃስ፣ የጌታን የትውልድ ሐረግ ከወንጌላውያን በተለየ መልክ አብዝቶ ስለመቍጠሩ እና ከታች ወደ ላይ ስለመጻፉም ሊቁ ቅዱስ ያሬድ፣ ከላይ የተመለከትነውን

(51) የአዳምን ዐፅም ወደ ኢየሩሳሌም ሲወስድ (የ15) ዓመት እድሜ የነበረው መልከጼዴቅ፣ ከኢየሩሳሌም ወደ አባቱና ወደ እናቱ ሳይመለስ በመቅረቱ እንጂ፣ አባትና እናት አለው አባቱም ቃይናም ይባላል፣ የጥር ገድለ አዳም፡፡



ታሪክና ምሥጢር፣ ከሉቃስ ወንጌል ወስዶ ሉቃስ ባህቲቱ ሐዲሳ ተናገረ እምካልዓን አንጎ ወእስከ አዳም አልዐለ፣ "ሉቃስ፣ ከጓደኞ ወንጌላውያን ብቻውን ተለይቶ አዲስ ነገርን ተናገረ፣ እስከ አዳ ድረስም ከፍ ከፍ አለ" ብሏል (የጥቅምት 22 ቀን መጽሐፈ ድጓ)፡፡

## ፊደል ስለነበራቸው እና ስላልነበራቸው ቋንቋዎች

መጽሐፍ እንደሚያስረዳን ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ (7) ዓመ ድረስ (አዳምና ሔዋን ዕፀ በለስን እስከበሉበት ጊዜ ድረስ) ሰው እንስሳ፣ አራዊትም ሁሉ በገነት ሳሉ አንዱ ከአንዱ ጋ ይነጋገሩበትና (ይግባቡበትና)፣ እግዚአብሔርም ሰውን ያነጋግርበ የነበረው አንድ የዕብራይስጥ ቋንቋ፣ ኩፋ. 5.1-3፣11.13-1 በአባቶቻችን ላይ የደረሰ የጥፋት ውሃ ዘፍ.7.11-23. በድጋሚ ወር እንዳያጠፋን ብለው በትዕቢት ተነሳስተው (43) ዓመት የመከላከ ሕንፃ ሠርተው የእግዚአብሔርን ኃይል በተፈታተኑ ስዎ ምክንያት፣ ዓለም በተፈጠረ (በ3510) ዓመት ራሱ የዕብራይስጡ ቋንቋ ጨምሮ (ለ72) ቋንቋ ተከፈለ ዘፍ.11.1-10፣ ኩፋ.10.10-17፡፡ ከእነዚህ (ከ72ቱ) ቋንቋዎች ውስጥም ፊደ የነበራቸውና ያልነበራቸው ነበሩ እነዚህም፡-

(1) በሴም ነገድ (25) ቋንቋዎች የነበሩ ሲሆን፣ ፊደል ያላቸ (8) ብቻ ናቸው እነዚህም ዓረቢ፣ ሶርያ፣ አጋዊ (ግእዝ) ዕብራዊ፣ ፋርሳዊ፣ ከለዳዊ፣ ህንዲና ሲኒ ይባላሉ፡፡

(2) በካም ነገድ (32) ቋንቋዎች የነበሩ ሲሆን፣ ፊደል ያላቸው ( ብቻ ናቸው እነዚህም ቅብጢ፣ ኖቢ፣ ባሻ፣ ቂልቂ፣ ፍልስጢ ቁብሻ ይባላሉ፡፡

(3) በያፌት ነገድ (15) ቋንቋዎች የነበሩ ሲሆን፣ ፊደል ያላቸ (6) ብቻ ናቸው እነዚህም ዮናኒ፣ ሮሚ፣ አፍርንጊ፣ ገርማ አርመኒና እንድልሽ ይባላሉ፡፡

(52) መጽሐፍ ቅዱስ፣ (ዕብ 7.1-4) የመልከጼዴቅ የትውልድ ቍጥር የለውም ለምን አለ →

www.ethiopianorthodox.org

በጠቅላላ አሁን ከተጠቀሱት (ከ72) ቋንቋዎችም፣ ፊደል የነበራቸው (20ዎቹ) ሲሆኑ (52ቱ) ፊደል የላቸውም ነበር፡፡ (ትርጓሜ ፊደልና መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ፣ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ዘኪዳነ ወልድ ክፍሌ)፡፡

፻፶፬፡-154 ዘንተ ስብሐተ ወዘንተ ማኅሌተ (ዘኒ ስብሐተ ወዘኒ ማኅሌተ)፣
ተአምርኪ ጸገየ ወፈረየ ሊተ፣
ከመ እሰብሕ ዳግመ እንዘ እጸውር ጸበርተ፣
ምስለ እለ ሐፀቡ አልባሲሆሙ በደመ በግዑ ድርገተ፣
ውስተ ባሕረ ማሕው ድንግል ክፍልኒ ቁመተ፡፡

ድንግል ሆይ ተአምርሽ፣ ፍጹም የሆነ ይህንን የማኅሌት ምስጋና አበበልኝ፣ አፈራልኝ (ለእኔ አብቦ አፈራ)፣ ዘንባባንም ይዤ ልብሳቸውን በበጉ ደም ከአጠቡ ጋር በአንድነት አመሰግን ዘንድ ብርሌን በሚመስል ባሕር ውስጥ መቆምን አድዪኝ፡፡ (በዕለተ ምጽአት ጊዜ በቀኝ መቆምን አድዪኝ)፡፡ (ሐተታ) ዘንባባን ይዤ አመስግን ዘንድ ማለቱ አብርሃም፣ ይስሐቅ ሲወለድና ጠላቶቹን ድል አድርጎ ሲመለስ ጌታን ለማመስገን ደስታውን የገለጸ ዘንባባን ይዞ ነውና ኩፋ 13.16-22፣ እንዲሁም ባለቤቷ ምናሴ ከሞተ ጀምሮ በብሕትውና (በብቸኝነት) በጾምና በጸሎት ተወስና የኖረች ዮዲት የምትባለዋ ዕብራዊት ሴት ሆሎሆርኒስ የተባለ የእስራኤልን ጠላት ድል አድርጋ ስትመለስ ከእስራኤል ልጆች ጋር ፈጣሪን ያመሰገነች የኃይልና የድል ምልክት የሆነ ዘንባባን ይዛ ነው መጽ.ዮዲ.8.2-7፣13.1-9፣15.12-13፡፡ (በ33) ዓ.ም መጋቢት (22) ቀን ማለትም የሆሣዕና በዓል በሚከበርበት ጊዜ ጌታን ለመቀበል የተሰበሰቡ ሰዎች፣ ያመሰገኑ በዘንባባ ነውና ዮሐ.12.13. ልብሳቸውን በበጉ ደም ከአጠቡ ጋር ማለቱም፣ ሰውነታቸውን እንደ መላእክት በኃጢአት ያላሳደፉ ሰማዕታት ራእ.7.13-15. ሰውነታቸውን ለመከራ አሳልፈው ሰጥተዉ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግደውን የእግዚአብሔርን በግ (እግዚአብሔር ወልድን) ዮሐ.1.29. አብነት አድርገዉ ደማቸውን አፈሰሱ ማለቱ ሲሆን፣ በንጹሕ

(53) መልከጼዴቅ፣ የትውልድ ቍጥር የለውም የተባለበት ምክንያት ካህን ሆኖ ሳለ በሌዋውያን መጽሐፍ ስለአልተጻፈ ነው ዕብ 7.1-4 ንባቡና ትርጓሜው፡፡



ባሕር ውስጥ መቆምን አድዪኝ ማለቱ ደግሞ፣ ደብረ ማሕው የምትባለዋ ቦታ በኢየሩሳሌም አጠገብ ያለችና ጌታ ቀድሞ በስደቱ ጊዜ ውሃን ያፈለቀባት ቦታ ናት ይህቺ ቦታም የገነትና የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ናትና ራእ. 15.2-5፡፡

፻፶፭፡-155 ኀብረ ሐመልሚል ቀይሕ ወፀዓድዒድ አርአያ ኰሰኰስ ዘብሩ
ተአምርኪ ንጹሕ በአምሳለ ወርቅ ግቡር፣
ተፈጸመ ናሁ ማኅሌተ ጽጌ ሥሙር፣
አስምኪ ቦቱ ንግሥተ ሰማይ ወምድር፣
ከመ በሕፅንኪ ያሰምክ ፍቁር፡፡

የሰማይና የምድር ንግሥት ማርያም ሆይ የብር ዝጕርጕር፣ የነጭና የቀይ ድብልቅ መልክ እንዳለው ጌጥ ንጹሕ የሆነ፣ (ሐሰት የሌለበት) ተአምርሽ፣ በወርቅ አምሳል የተዘጋጀ ሆኖ ያማረና የተወደደ ማኅሌተ ጽጌ የተባለ ምስጋና እነሆ ተፈጸመ፣ የተወደደ ልጅሽ በእቅፍሽ ውስጥ እንዳለ ይህንን የማኅሌተ ጽጌ ምስጋናን ተቀብለሽ ወደእሱ አድርሺ፡፡ (ሐተታ) ተአምርሽ የብር ዝጉርጉር፣ የነጭ እና የቀይ ድብልቅ ነው ማለቱ፣ የእመቤታችን ተአምር በብዙ መልክ ስለሚገለጽ ነው፡፡

፻፶፮፡-156 መኑ እንበለ ጽጌኪ (መኑ ጠቢብ እንበለ ጽጌኪ) ዘየአምር ጥዩ፦
ከዋክብተ ሰማይ ኍልቆ ወኖፃ ባሕር ድቁቀ፣
ለውዳሴኪ ማርያም ከመ ለብሐዊ ዘጽሕቀ፣
እስመ ኢንክል ፈጽሞ ተአምረኪ ጥንቁቀ፣
ናርምም ስብሐተኪ ነጊረነ ሕቀ፡፡

ማርያም ሆይ ጠቢቡ ሲራክ የጌታ የኃይሉን ከሃሊነት መጥኖ ያወቀ ማነው? ቸርነቱንስ ፈጽሞ መናገር የሚችል ማነው? ብሎ እንደተናገረ ሲራ.18.4-6. የሰማይ ከዋክብትንና የደቀቀ (ስፍር ቍጥር የሌለው) የባሕር አሸዋን ከልጅሽ በቀር ጠንቅቆ የቈጠረና ያወቀ ጥበበኛ ማነው? (ምንስ ጠቢብ አለ?) ብርሌ ሠሪ የሆነ ቅዱስ ኤፍሬም በበኩሉ

(54) መልከጼዴቅ፣ የብሉይ ኪዳን የመጀመሪያው ካህን በመሆኑ፣አዲስ ኪዳንን ለመሠረተ ለኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ሆኗል ዘፍ 14.18-20፣ መዝ.109.4፣ ዕብ.7.20-26፡፡

www.ethiopianorthodox.org

*ውዳሴ ማርያም በተባለ ድርሰቱ የእሱን (የጌታን) የገናንነቱን ታላቅነት ጠንቅቀን መናገር አይቻልምና እንዳለ፣ ተአምርሽን ጠንቅቆ መናገር እና መጨረስ አይቻለንምና፣ ከምስጋናሽ ጥቂቱን ነግረን ዝም እንበል፡፡*

**ቅዱስ ኤፍሬም፣ የድንግል ማርያምን ውዳሴ መቼ ደረሰ?**

(ታሪክ) ቅዱስ ኤፍሬም (በ306) ዓ.ም ገደማ ከዋክብትን ከሚያመልኩ ሰዎች ተወለደ አገሩ ሶርያ ነው አባቱም የጣዖት ካህን ነበር፣ በወጣትነቱም ንጽቢን ለምትባል አገር ጳጳስ ወደ ነበረው ወደ ያዕቆብ ሄዶ ተምሮ ተጠመቀ (የ19) ዓመት ወጣትም ሆኖ (በ325) ዓ.ም በተደረገው በኒቅያ ጉባኤ ላይ መምህሩ ያዕቆብን ተከትሎ ሄዷል በኋላም ከቂሣርያ ሊቀ ጳጳስ ከቅዱስ ባስልዮስ የዲቁና መዓርግን ተቀበለ፣ ትንሽ ጊዜም ቆይቶ ቅስናን ተቀብለ፣ ብዙ ተአምራትንም አድርጓል ብዙ ድርሳናትንና ተግሣጻትንም ደርሷል፣ ጽፏልም፣ ከብዙ ድርሰቱም አንዱ ከሰኞ እስከ እሑድ የሚጸለየው የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ውዳሴ (ምስጋና) ነው ውዳሴዋን የደረሰውም መንፈስ ቅዱስ ገልጸለት በእድሜዋ መጠን (64) አድርጐ ሲሆን ዘመኑም (በ364) ዓ.ም ገደማ ነው (የሐምሌ 15 ቀን መጽሐፈ ስንክሳርና የተለያዩ የታሪክ መጻሕፍት)፡፡

፻፶፯157 ስብሐት ለአብ ወለወልድ አእኰቶ፣
ወለመንፈስ ቅዱስ ሰላም ዘአክህለኒ ፈጽሞቶ፣
ለተአምርኪ ድንግል ለለጊዜ ወጠንኩ አንብቦቶ፣
በጽድቅኪ ለእገርየ ሠርሒ ፍኖቶ፣
ወለልቡናየ ፈጽሚ ተምኔቶ፡፡

*ለአብ ምስጋና ይገባል፣*
*ለወልድም ምስጋና ይገባል፣*
*አስጀምሮ ለአስፈጸመኝ ለመንፈስ ቅዱስም ምስጋና ይገባል፡፡*
*ድንግል ሆይ ተአምርሽን በማነብበት ጊዜ ሁሉ የእግረ ልቡናዬን መንገድ አቃኝልኝ፣ የልቡናዬንም በጎ ሐሳብ ፈጽሚልኝ፡፡*

(55) ሰይፍ (የጦር መሣሪያ) መሥራትና መገዳደል የተጀመረው በቃኤልና በልጆቹ ነው ዘፍ.4.8-9 እና ቀኵጥር 22፣ መጽ ሄኖ.19.20፡፡



፻፶፰፦158 ስብሐት ለኪ ማርያም በጽጌ መላእክት ትጉሃን፣
ስብሐት ለኪ ማርያም በጽጌ ነቢያት ቅዱሳን፣
ስብሐት ለኪ ማርያም በጽጌ ሐዋርያት ሰባክያን፣
ስብሐት ለኪ ማርያም በጽጌ ሰማዕት ወጻድቃን፣
ወስብሐት ይደሉ ለማኅሌተ ጽጌኪ ወይን፣
እስመ በማኅሌተ ጽጌኪ ወይን ይትፌሣሕ ኀዙን፡፡

*ማርያም ሆይ ትጉሃን መላእክት በሚያቀርቡልሽ ምስጋና አመሰግንሻለሁ*
*ቅዱሳን ነቢያት በሚያቀርቡልሽ ምስጋና አመሰግንሻለሁ፣*
*ወንጌልን ያስተማሩ ሐዋርያት በሚያቀርቡልሽ ምስጋና አመሰግንሻለሁ፣*
*ስለ ሃይማኖት የተጋደሉና የመሰከሩ ጻድቃንና ሰማዕታት በሚያቀርቡልሽ ምስጋና አመሰግንሻለሁ፣*
*የልጅሽ የደሙ ምሳሌ በሆነውና ማኅሌተ ጽጌ በተባለ ምስጋና ለቀረ ወይንም፣ ምስጋና ይገባል፣*
*በልጅሽ ደም እና ማኅሌተ ጽጌ በተባለ ምስጋና፣ በቀረበ ወይንም ክብር ይገባል ያዘነ፣ የተከዘ ይደሰታልና መዝ 103.15፣ ምሳ 31.6-7፡፡*

***አነሳስቶ ላስጀመረን፣ አስጀምሮም ላስፈጸመን ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ይግባውና፣ የመጨረሻውና ክፍል ሦስት ማኅሌተ ጽጌ በዚህ ተፈጸመ፡፡***

(56) ጌታ፣ ሰይፍን ያነሱ በሰይፍ ይሞታሉ ሲል በቅዱስ ጴጥሮስ አማካኝነት ትዕግሥትን አስተማረ ዮሐ 18.10-12፡፡

www.ethiopianorthodox.org

- ማኅሌተ ጽጌ ግእዝ ትንሣኤ ዘጉባኤ 1941 ዓ.ም አዲስ አበባ፣
- በአክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ ተዘጋጅቶ በጠቅላይ ቤተክህነት ጽ/ቤት መጋቢት (24) ቀን 1943 ዓ.ም በትንሣኤ ዘጉባኤ የታተመ መርሐ ልቡና የተባለ መጽሐፍ፣
- መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ኪዳነ-ወልድ ክፍሌ 1948 ዓ.ም
- የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ አዘጋጅ አባ ጎርጎርዮስ ሊቀጳጳስ 1974
- የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት አማርኛ 1974 ዓ.ም
- መጽሐፍ ቅዱስ (81) አማርኛ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ 1980 ዓ.ም፣
- ቅዱስ ወንጌል ንባቡና ትርጓሜው ትንሣኤ ዘጉባኤ 1980 ዓ.ም፣
- የ14ቱ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው ትንሣኤ ዘጉባኤ 1980 ዓ.ም፣
- የውዳሴ ማርያም አንድምታ ትርጉም ትንሣኤ የመጻሕፍት አሳታሚ ድርጅት 1983 ዓ.ም፣

(57) ንጉሥ ሰሎሞን፣ የእግዚአብሔርን ቤት እስኪሠራ ድረስ መዘምራኑ፣ ጌታ ¹ይመስገንበት በነበረው ድንኳን ፊት በዜማ ያመሰግኑ ነበር 1ኛ.ዜና.6.31-33።



- መኃልየ ሰሎሞን ንባቡና ትርጓሜው ትንሣኤ ዘጉባኤ 1988 ዓ.ም፣
- ባለ (402) ተአምር፣ተአምረ ማርያም ተስፋ ገብረ ሥላሴ 1988 ዓ.ም፣
- ድርሳን፣ ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ንባቡና ትርጓሜው ትንሣኤ ዘጉባኤ 1987 ዓ.ም
- ባለ (111) ተአምር፣ ተአምረ ማርያም ትንሣኤ ዘጉባኤ 1989 ዓ.ም
- መጽሐፈ ሰዓታት ዘደብር ዓባይ ግእዝ አዘጋጅ ሊቀ ሥልጣናት አባ ጥዑመ ልሳን አክሱም ማተሚያ ቤት 1992 ዓ.ም
- መጽሐፈ ስንክሳር ግእዝና አማርኛ እትም 1993 እና 1994 ዓ.ም ትንሣኤ ዘጉባኤ
- ራእየ ዮሐንስ፣ ንባቡና ትርጓሜው ትንሣኤ ዘጉባኤ 1994 ዓ.ም ባለ 150 ተአምር፣ተአምረ ኢየሱስ ትንሣኤ ዘጉባኤ 1994 ዓ.ም
- መጽሐፈ ኢሳይያስ ንባቡና ትርጓሜው አዘጋጅ ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ የ4ቱ ጉባኤ ቤት መምህር
- 1996 ዓ.ም ጎንደር ማተሚያ ቤት
- የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ንባቡና ትርጓሜው 1996 ዓ.ም ትንሣኤ ዘጉባኤ

(58) የእግዚአብሔር መዝሙር፣ በተጀመረ ጊዜ ጉባኤው ሁሉ ሰገዱ፣ መዘምራኑም ዘመሩ 2ኛ.ዜና.29.25-28። ከብዙ ሺህ እስራኤላውያንም ውስጥ፣ ብዙ ወንዶችና ብዙ ሴቶች መዘምራን ነበሩ መጽ.ነህ.7.68።

www.ethiopianorthodox.org

መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ፡- መርሐ መጻሕፍት በሊቀ ሊቃውንት ያሬድ ሽፈራው የቅኔ እና የመጻሕፍተ ሐዲሳት ትርጓሜ መምህር ባህርዳር ማተሚያ ቤት 1997 ዓ.ም

- መጽሐፈ ዳንኤል እና የ12ቱ ደቂቀ ነቢያት መጽሐፍ ንባቡና ትርጓሜው ትንሣኤ ዘጉባኤ 1998 ዓ.ም
- የዓመተ ዓለም አቈጣጠር የ12ቱ ደቂቀ ነቢያት ትርጓሜ መግለጫ (መግቢያ) 1998 ዓ.ም ትንሣኤ ዘጉባኤ
- ዝክረ ቅዱሳን፣ ዘተዋሕዶ አማርኛ 1ኛ መጽሐፍ ሚያዝያ 2000 ዓ.ም በአዜብ በርሄ ሜጋ ማተሚያ ቤት
- መጽሐፈ ቀሌምንጦስ፣ግእዝና አማርኛ አዘጋጅ ገብረ ዮሐንስ ገብረ ማርያም ሐምሌ 2000 ዓ.ም
- መልክአ ጉባኤ (ግእዝ ማኅሌተ ጽጌ) አዘጋጅ መጋቤ አእላፍ ሄኖክ ወልደ ሚካኤል በጎንደር የደብረ ኃይልና የደብረ ጥበብ በአታ ለማርያም የአቋቋም ምስክር ጉባኤ ቤት መምህር 2002 ዓ.ም ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣
- ገድለ አዳም አማርኛ አሳታሚ በኢ/ኦ/ተ/ቤተክርስቲያን የሰ/ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን 2002 ዓ.ም አዲስ አበባ፣
- ዩርማኖስ እና ጳላድዮስ የሚባሉ ጸሐፍያን የጻፉት ዜና አበው የተባለ መጽሐፍ::

(59) የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማራቸው ብቻ ወደ ወኅኒ የወረዱት ቅዱስ ጳውሎስ እና ሲላስ፣ በዜማ ያመሰግኑ ነበር የሐዋ.16.19-27::



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ የተመረመሩ ማለትም፡-

**ክፍል አንድ ማኅሌተ ጽጌ** ከያዛቸው (29) ርእሶች ውስጥ ተአምረ ማርያም ለመጀመሪያ ጊዜ በየት ተዘጋጀ?
ሰዓታት ማለት ምን ማለት ነው?
ለምንስ ሰዓታት ተባለ?
የመጀመሪያው ሠዓሊና ባለ ዘውድ ሰው ማን ነበር?
ይስሐቅ በስንት ዓመቱ ሊሰዋ ቀረበ?
ትምህርተ ኅቡኣት ማለት ምን ማለት ነው? ለምንስ ዚቅ የለውም? የሚሉትንና (የ255) የግእዝ ስንኞች ትርጉምና ምሥጢር፣ (100) መጽሐፍ ቅዱሳዊ የግርጌ ማስታዎሻዎችንና ልዩ ልዩ ታሪኮችን ይዞ መታተሙን፣

**ክፍል ሁለት ማኅሌተ ጽጌ** በበኩሉ፣ ከያዛቸው (44) ርእሶች ውስጥ የወርቅ ቀለበት በሰማይ፣ የሰብአ ሰገል ቍጥር ስንት እንደሆነ፣ የሃሌ ሉያ ትርጉምና የሃሌታ ምንነት? ዝርዝር ምሥጢርን፣ (የ7ቱ) ኪዳናትን ዝርዝር ምሥጢር፣ ግእዝ ኪዳን የሚደረስባቸው ቀኖችን እና ምሥጢራቸውን፣ (የ263) የግእዝ ስንኞችን ትርጉምና ምሥጢርን፣ (83) መጽሐፍ ቅዱሳዊ የግርጌ ማስታዎሻዎችን ይዞ፣ መታተሙን በዚህ እየገለጽን አሁን ደግሞ፡-

**ክፍል ሦስት ማኅሌተ ጽጌ** (የ287) የግእዝ ስንኞችን ትርጉምና ምሥጢር፣ የሞቱና ያልሞቱ ሰዎች በዓይን ስለመተያየታቸው፣ በዓለም የመጀመሪያው ጸሐፊ ማን ነበር? ጌታ የባረካቸው ሕጻናት ምን ሆኑ?
ጌታ ያታቀፈው ሕጻንስ ልዩ ስም ማነው? ፊደል መቼና በማን መጣ? የሚሉትንና (የ22ቱ) አርእስተ አበውን ስም ዝርዝርና ታሪካቸውን፣ (ከ33) ርእሶች ጋር (59) መጽሐፍ ቅዱሳዊ የግርጌ ማስታዎሻዎችን ይዞ መቅረቡን ስናበሥር በደስታ ነው::

እግዚአብሔር አምላክ ኢትዮጵያን፡-
ይባርክ፣ ሕዝቧንም ይጠብቅ::
መልካም ንባብ!!

www.ethiopianorthodox.org

0911-212365 (011-127-29-47)

ዋጋ፡ 40.00
$ 10:00